በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

የበጎ አድራጎት ድርጅቶች የፕሮጀክት አፈጻጸምና ክትትልን በተመለከተ የተከናወነ የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት

ጥር 2006 ዓ.ም

አዲስ አበባ

ማውጫ

ማውጫ 1
ክፍል አንድ 1
መግቢያ 1
የኤጀንሲው ዓላማ፣ ስልጣንና ተግባር 2
የቦርዱ ስልጣንና ተግባር 2
የኤጀንሲው ስልጣንና ተግባር 3
የኤጀንሲው አደረጃጀት እና የሰው ኃይል 3
የኤጀንሲው የፋይናንስ ምንጭ 4
የበጎ አድራጎት ድርጅቶች እና ማኀበራት ኤጀንሲ የድጋፍና ክትትል ተግባር የአሰራር ስርዓት መግለጫ (Process description) 4
የኦዲቱ ዓላማ 5
ለኦዲት የተመረጠው የኦዲቱ አካባቢ 5
የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫዎች 5
የኦዲት የመመዘኛ መስፈርት 6
የኦዲቱ ወሰንና ዘዴ 6
ክፍል ሁለት 8
የኦዲት ግኝቶች 8
I. የበጎ አድራጎት ድርጅቶች የፕሮጀክት አፈፃፀም፣ ክትትልና ቁጥጥር በተመለከተ የወጡ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎችን ማስፈፀም የሚያስችል የአሠራር ሥርዓት መዘርጋቱን እና ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ፤ 8
የበጎ አድራጎት ድርጅቶችን የፕሮጀክት አፈፃፀምና ክትትል በተመለከተ፤ 8
ኤጀንሲው በዴስክና በመስክ ላደረጋቸው የክትትል ሪፖርቶች ግብረ መልስ መስጠቱን በተመለከተ.. 10
የበጎ አድራጎት ድርጅቶች የዓላማ ማስፈፀሚያና አስተዳደራዊ ወጭ በመመሪያው መሰረት መፈፀሙን በተመለከተ፣ 11
የበጎ አድራጎት ድርጅቶች የዓላማ ማስፈፀሚያና የአስተዳደራዊ ወጪን ለማስፈፀም የወጣውን ክፍፍል በተመለከተ 13
ኤጀንሲው ለገቢ ማስገኛ እና ለህዝባዊ መዋጮ ፈቃድ የሰጣቸውን በጎ አድራጎት ድርጅቶች በተመለከተ 14
ከውጭ ምንጭ ከ10 በመቶ በላይ ገቢ ማግኘት ስለማይችሉ የኢትዮጵያ በጎ አድራጎት ድርጅቶች በተመለከተ 15

በጎ አድራጎት ድርጅቶች የፕሮጀክት ፕሮፖዛል ግምገማን በተመለከተ 16

የበጎ አድራጎት ድርጅቶች የፕሮጀክት አፈፃፀም ለመከታተል የሚያስችል መመሪያ መኖሩን በተመለከተ፣........ 17

በዳግም ምዝገባ ያልተመዘገቡ ድርጅቶችን በተመለከተ 19

በክልሎች የበጎ አድራጎት ድርጅቶችን ለማስተዳደር የሚያስችል ህጋዊ ማዕቀፍ መኖሩን በተመለከተ 20

ኤጀንሲው ለበጎ አድራጎት ድርጅቶች እና ማህበራት ስልጠና መስጠቱን በተመለከተ፣........ 21

II. የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራትን አዋጅ፣ ደንብ እና መመሪያዎችን ተፈጻሚ የሚያደርጉ የዘርፍ አስተዳዳሪዎች፣ ክልሎች እና ባለድርሻ አካላት በቅንጅት የሚሰሩበት የአሰራር ስርዓት እና ቀልጣፋ የመረጃ ልውውጥ ስርዓት እንዲሁም መደበኛ የመወያያ መድረክ የተዘረጋ እና ተግባራዊ የተደረገ መሆኑን በተመለከተ፤ 22

ኤጀንሲው ከዘርፍ አስተዳዳሪዎችና ከክልል አስፈፃሚ አካላት ጋር የመግባቢያ ሰነድ(memorandem of understanding) ያለው መሆኑን በተመለከተ፤........ 22

ኤጀንሲው ከባለድርሻ አካላት ጋር ስላለው የጋራ መድረክ እና ክትትል በተመለከተ........ 24

የበጎ አድራጎት ድርጅቶች መረጃ አያያዝን በተመለከተ 25

ክፍል ሶስት........ 27

መደምደሚያ 27

ክፍል አራት 30

የማሻሻያ ሃሳቦች........ 30

አባሪ 1 የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማኅበራት ኤጀንሲ ድርጅታዊ መዋቅር 34

አባሪ 2 የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች (Evaluative Criteria) 35

አባሪ 3 በዝርዝር ኦዲት በመስክ የታዩ የዘርፍ አስተዳዳሪዎችና በጎ አድራጎት ድርጅቶች........ 37

አባሪ 4 በኦዲት ወቅት ፋይላቸው የታዩ በጎ አድራጎት ድርጅቶች ዝርዝር 38

Ethiopian Charity 38

Foreign Charities........ 40

Adoption 40

አባሪ 5........ 41

የበጎ አድራጎት ድርጅቶች እና ማኅበራት ኤጀንሲ የድጋፍና ክትትል ተግባር የአሰራር ስርዓት ሥዕላዊ መግለጫ (Process description)........ 41

አባሪ 6 የማሪስቶፕስ ኢንተርናሽናል የ2012 እና 2011 የሂሳብ ትንታኔ........ 42

ኪውር ኢንተርናሽናል የ2012 የሂሳብ ትንታኔ 43

ክፍል አንድ

መግቢያ

1. በኢትዮጵያ ዘመናዊ የመንግስት አስተዳደር ህግና ስርዓትን በተከተለ መልኩ በጎ አድራጎት ድርጅቶችንና ማህበራትን መመዝገብ፣ ማስተዳደርና መቆጣጠር የተጀመረው በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግስት ሲሆን፣ በወቅቱ የአገር ግዛት ሚኒስቴር ተብሎ ይጠራ የነበረው መንግስታዊ ተቋም በ1952 ዓ.ም በወጣው የፍትሐብሔር ሕግ ከቁጥር 404 - 549 ባሉት ድንጋጌዎችና እነዚህን ድንጋጌዎች በዝርዝር ለማስፈፀም በ1959 ዓ.ም በወጣው የማህበራት ምዝገባ ደንብ ቁጥር 321/1959 መሠረት የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራትን ሲመዘግብ ቆይቷል፡፡
2. በደርግ ዘመነ መንግስት የአገርና የህዝብ ደህንነት ጥበቃ ሚኒስቴር በአዋጅ ቁጥር 179/1972 አንቀፅ 17 መሰረት ዓላማቸው ትርፍ ለማግኘት ያልሆኑ ማኅበራትን ይመዘግብና ይቆጣጠር የነበረ ሲሆን፣ በ1980 የኢትዮጵያ ህዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መስተዳድርን ስልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 8/1980 መሰረት የአገር ውስጥ ጉዳይ ሚኒስቴር ይህንን ስራ ሲሰራ ቆይቷል፡፡
3. ከ1983 የመንግስት ለውጥ በኋላ የመደራጀት መብት በህግ በመረጋገጡ በርካታ የአገር ውስጥና የውጭ በጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ተቋቁመው በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛሉ፡፡ ከ1983-1987 ዓ.ም የበጎ አድራጎት ድርጅቶችንና ማህበራትን የመመዝገብ፣ ማስተዳደርና መቆጣጠር የአገር ውስጥ ጉዳይ ሚኒስቴር ተብሎ በሚጠራው የመንግስት አካል ሲከናወን የነበረ ሲሆን ከ1987 በኋላ የኢፌዲሪ አስፈፃሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 4/1987 እንዲሁም ይህን አዋጅ ባሻሻለው አዋጅ ቁጥር 471/1998 አንቀጽ 23 በተደነገገው መሰረት የኢፌዲሪ የፍትህ ሚኒስቴር ዓላማቸው ለትርፍ ያልሆነ የውጭ ድርጅቶችን፣ ስልጣኑ በህግ ለሌላ የመንግስት አካል ካልተሰጠ በስተቀር እንቅስቃሴያቸው በአዲስ አበባ እና በድሬዳዋ ከተሞች የሆነ ወይም በአንድ ክልል ብቻ ያልተወሰነ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን፣ ማህበራትን እና የሃይማኖት ድርጅቶችን እንዲመዘግብ ስልጣን ተሰጥቶታል፡፡
4. ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ከላይ በተጠቀሰው አዋጅ መሰረት የተሰጠውን ተግባር ለማከናወን በጣም ውስን የሰው ኃይል የያዘ የማህበራት ምዝገባ ጽ/ቤት ያደራጀ ቢሆንም የአገልግሎት አሰጣጡ የደንበኞችን ፍላጎት መሰረት ያላደረገ፣ እያንዳንዱ በጎ አድራጎት ድርጅትና ማህበር የሚሰራውን ሥራ ለመገምገም የሚያስችል የአሰራር፣ የክትትልና ድጋፍ መስጫ ስርዓት

ያልነበረ፣ ህግን አክብረው በማይንቀሳቀሱት ላይ ተገቢውን እርምጃ ለመውሰድ የሚያስችል በቂ የህግ ማዕቀፍ የሌለ በመሆኑ ችግሮቹን ለመፍታት የሚያስችል አዋጅ ቁጥር 621/2001 እንዲወጣ ተደርጓል፡፡

5. በዚሁ አዋጅ አንቀፅ 8 መሠረት በመንግስት በተሰየሙ ሰባት አባላት በሚመራ ቦርድ የሚተዳደር የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማኅበራት ኤጀንሲ እንደ አንድ የፌደራል የመንግስት መስሪያ ቤት ለፍትህ ሚኒስቴር ተጠሪ ሆኖ በመቋቋም ከመስከረም 2002 ጀምሮ በአዋጁ የተቀመጡትን ተልዕኮዎች ለመፈጸም እየሰራ ይገኛል፡፡ የፌደራል አስፈጻሚ አካላትን እንደገና ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 691/2003 የኤጀንሲው ተጠሪነት ለፌደራል ጉዳዮች ሚኒስቴር እንዲሆን ተደርጓል፡፡

የኤጀንሲው ዓላማ፣ ስልጣንና ተግባር

የኤጀንሲው ዓላማዎች

6. ኤጀንሲው በአዋጅ ቁጥር 621/2001 መሰረት የሚከተለው ዓላማ እንዲኖረው ተደርጓል፣

- የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማኀበራት እንዲስፋፉና ተልዕኳቸውን በሕግ መሰረት እንዲወጡ ማስቻልና ማበረታታት፤
- የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማኀበራት አሰራር ግልፅነት እና ተጠያቂነት የሰፈነበት ሊሆን የሚችልበትን ሁኔታ መፍጠር፤
- የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማኀበራት በሕግ መሰረት መስራታቸውን ማረጋገጥ፡፡

የቦርዱ ስልጣንና ተግባር

7. ቦርዱ በአዋጅ ቁጥር 621/2001 መሰረት የሚከተለው ስልጣንና ተግባር ተሰጥቶታል፣

ሀ/ ከዚህ አዋጅ አፈጻጸም ጋር ተያይዞ የሚነሱ የፖሊሲ ጉዳዮችን መርምሮ የውሳኔ ሀሳብ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፣

ለ/ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች እና ማኅበራት አስተዳደርን በተመለከተ ለሚያጋጥሙ ችግሮች መፍትሄ ይሰጣል፣

ሐ/ የኤጀንሲው ዋና ዳይሬክተር በሚሰጠው ውሳኔ ላይ በዚህ አዋጅ መሰረት የሚቀርቡ ይግባኞችን መርምሮ ይወስናል፣

መ/ በዚህ አዋጅ መሰረት በኤጀንሲው የሚወጡ መመሪያዎችን መርምሮ ያጸድቃል፣

ሠ/ በዋና ዳይሬክተሩ የሚቀርቡለትን የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማኀበራትን የሚመለከቱ

ሌሎች ጉዳዮች መርምሮ ይወስናል፡፡

የኤጀንሲው ስልጣንና ተግባር

8. ኤጀንሲው በአዋጅ ቁጥር 621/2001 መሠረት የሚከተለው ስልጣንና ተግባር ተሰጥቶታል፤

ሀ/ ለበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማኅበራት ፈቃድ መስጠት፣ መመዝገብና መቆጣጠር፤

ለ/ የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማኅበራት የተሻለ አሰራር እንዲኖራቸው ማበረታታት፤

ሐ/ ከሥልጣንና ተግባሩ ጋር ግንኙነት ያላቸውን መረጃዎች ማሰባሰብ፣ መተንተንና ማሰራጨት፤

መ/ የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማኅበራትን ምዝገባ በሚመለከት መረጃ በጋዜጣ ማሳተምና ማሰራጨት፤

ሠ/ የመንግስት አካላት እና የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማኅበራት የሚሳተፉባቸውን የምክክር መድረኮች ማዘጋጀት፤

ረ/ ዓላማውን ለማሳካት □ሚያስችል የውሳኔ ሀሳብ ለሚኒስቴሩ ማቅረብ፤

ሰ/ ለምዝገባና ፈቃድ ጥያቄ የሚያቀርቡ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ወይም ማኅበራት ጉዳይ ከሚመለከታቸው የዘርፍ አስተዳዳሪዎች ጋር በመመካከር መርምሮ መወሰን፤

ሸ/ ስለ ሰነዶች ማረጋገጥና ምዝገባ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የዘለቄታ በ□ አድራጎት እና የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅት ሰነዶችን ማረ□□ጓና መመዝገብ፤

ቀ/ ለሚሰጣቸው አገልግሎቶች በመንግስት በሚፀድቀው ተመን መሰረት የአገልግሎት ክፍያዎችን መሰብሰብ፤

በ/ የንብረት ባለቤት መሆን፣ ውል መዋዋል፣ በራሱ ስም መክሰስና መከሰስ፤

ተ/ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በአዋጁ የተሰጡትን ስልጣንና ተግባራት በውክልና መስጠት፣ እና

ቸ/ ዓላማዎቹን ለማሳካት አስፈላጊ የሆኑ ሌሎች ተግባሮችን መፈፀም፤

የሚሉ ናቸው፡፡

የኤጀንሲው አደረጃጀት እና የሰው ኃይል

<u>የኤጀንሲው አደረጃጀት</u>

9. ኤጀንሲው በቦርድ የሚተዳደር ሲሆን ለቦርዱ ተጠሪ የሆነ አንድ ዋና ዳይሬክተርና በስሩ አንድ የዋና ዳይሬክተር ረዳት አለ፤ እንዲሁም ተጠሪነታቸው ለዋና ዳይሬክተሩ የሆኑ የፈቃድና ምዝገባ ዳይሬክቶሬት፤ የክትትልና ድጋፍ ዳይሬክቶሬት፤ የንብረት ማጣራት፣ ማስተላለፍና ማስወገድ ዳይሬክቶሬት፤ የኮምዩኒኬሽን የስራ ሂደት፤ የእቅድና የሀብት አስተዳደር የስራ ሂደት፤ የሰው ሀብትና ለውጥ ስራ አመራር ጽ/ቤት እንዲሁም የውስጥ ኦዲት አገልግሎት ክፍሎች አሉት፡፡ (አባሪ 1)

<u>**የኤጀንሲው የሰው ኃይል**</u>

10. ኤጀንሲው በመጋቢት ወር 2005 ዓ.ም በጠቅላላው 109 ሰራተኞች የነበሩት ሲሆን ከነዚህ ውስጥ 55ቱ (50.4%) ሴቶች ሲሆኑ 54ቱ(49.6%) ወንዶች ናቸው፡፡ የሰራተኞች ፕሮፋይል በትምህርት ደረጃ ሲታይ በኤም.ኤስ.ሲ/ኤም.ኤ ደረጃ ያሉ 3 (2.8%)፣ የመጀመሪያ ዲግሪ ያላቸው 52(47.7%)፣ ኮሌጅ ዲፕሎማ/10^{+3}፣ 10^{+2}/ 26 (23.9%)፣ ከ9ኛ-12ኛ ክፍል ያሉ 14 (12.8%) እንዲሁም ከሁለተኛ ደረጃ በታች ያሉ ሰራተኞች 7 (6.4%) ናቸው፡፡

የኤጀንሲው የፋይናንስ ምንጭ

11. የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማኅበራት ኤጀንሲ ስራውን የሚያከናውነው ከመንግስት በሚመደብለት በጀት ሲሆን ከ2002-2005 የተመደበለት በጀትና የወጣው ወጭ በሚከተለው ሰንጠረዥ ተመልክቷል፡፡

በጀት ዓመት	ተፈቀደ በጀት	ስራ ላይ የዋለ በጀት	ሥራ ላይ የዋለው በመቶኛ
2002	8,540,038.60	6,289,314.77	(74%)
2003	5,475,679.53	4,910,630.69	(90%)
2004	9,985,553.60	7,380,675.46	(74%)
2005	11,904,420.00	9,278,397.00	(78%)

የበጎ አድራጎት ድርጅቶች እና ማኅበራት ኤጀንሲ የድጋፍና ክትትል ተግባር የአሰራር ስርዓት መግለጫ (Process description)

12. የበጎ አድራጎት ድርጅቶች እና ማኅበራት ኤጀንሲ ከበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማኅበራት የድጋፍ ጥያቄ ሲቀርብለት ማመልከቻ በመቀበልና ድጋፍ የሚደረግበትን ጉዳይ በመለየት የተለያዩ ድጋፎችን ይሰጣል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ከህብረተሰቡ የሚገኘውን ጥቆማ፣

በየዓመቱ የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማኅበራት በሚያቀርቡት የሥራና የኦዲት ሪፖርት ግኝት መነሻነት የፋይልና የመስክ ምርመራና ግምገማ በማድረግ ውሳኔ ይሰጣል፡፡

13. በአጠቃላይ የስራ ሂደቱ የክትትል ተግባርን በሕግ እና የሥራ ሂደቱ ባለቤት በሚያስቀምጣቸው መመሪያዎች መሰረት ይፈፅማል፤ ማንኛውም አካል የሚያቀርበውን ጥቆማ በመቀበል የፋይል ምርመራ ያካሂዳል፤ የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማኅበራት በህግ አግባብ፣ በተቋቋሙበት ዓላማ መሰረትና ባቀረቡት ፕሮጀክት ፕሮፖዛል መሰረት መንቀሳቀሳቸውን ይከታተላል፣ ህጋዊ እርምጃ ይወስዳል፡፡ ሥዕላዊ መግለጫው በአባሪ 5 ተያይዟል፡፡

የኦዲቱ ዓላማ

14. የኦዲቱ ዓላማ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ፕሮጀክት አፈፃፀምና ክትትል ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋና ውጤታማ መሆኑን፣ እንዲሁም ኤጀንሲው ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት እየሰራ መሆኑን፣ ተመጋጋቢ የሆነ የመረጃ ልውውጥ ስርዓት መዘርጋቱን እና ተግባራዊ መደረጉን ለመገምገም ሲሆን ከዚህ ጋር በተያያዘ በኤጀንሲው ላይ የሚታዩ የአሰራር ችግሮች ካሉ ችግሮቹን እና መንስዔዎቻቸውን በመለየት ችግሮቹን ለማስወገድ ወይም ለማቃለል የሚረዱ የማሻሻያ ሃሳቦችን ለማቅረብ ነው፡፡

ለኦዲት የተመረጠው የኦዲቱ አካባቢ

15. ለክዋኔ ኦዲቱ የተመረጠው የኦዲት አካባቢ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች የፕሮጀክት አፈፃፀም እና ክትትል ኢኮኖሚያዊ፤ ቀልጣፋ እና ውጤታማ መሆኑን መገምገም የሚል ነው፡፡

የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫዎች

16. ከላይ የተመለከተውን የኦዲት ዓላማ ለማሳካት ሁለት የኦዲት ትኩረት አቅጣጫዎች (Audit Issues) የተለዩ ሲሆን በመጀመሪያው የትኩረት አቅጣጫ ሥር ሁለት ንዑስ የትኩረት አቅጣጫዎች ተቀምጠዋል፡፡ እነሱም:-

   1. ኤጀንሲው የበጎ አድራጎት ድርጅቶች የፕሮጀክት አፈፃፀም፣ ክትትልና ቁጥጥር በተመለከተ የወጡ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎችን ማስፈፀም የሚያስችል ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋና ውጤታማ የአሰራር ስርዓት መዘርጋቱን እና ተግባራዊ መደረጉን መገምገም፡፡

1.1 ኤጀንሲው የበጎ አድራጎት ድርጅቶች በየበጀት ዓመቱ ክትትልና ቁጥጥር የሚያደርግበት ስርዓት የዘረጋ እና ተግባራዊ ያደረገ መሆኑን መገምገም፣

1.2 የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ከሚመለከተው የመንግስት አካል ጋር የፕሮጀክት ስምምነት ማድረጋቸውን እና በገቡት የፕሮጀክት ስምምነት መሰረት የፕሮጀክት አፈፃፀማቸው ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋና ውጤታማ መሆኑን መገምገም፣

2. የበጎ አድራጎት ድርጅቶችንና ማህበራት ኤጀንሲ፤ አዋጆችን፣ ደንቦችን እና መመሪያዎችን ተፈጻሚ የሚያደርጉ የዘርፍ አስተዳዳሪዎች፣ ክልሎች እና ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት የሚሰሩበት የአሰራር ሥርዓት እና ቀልጣፋ የመረጃ ልውውጥ ሥርዓት እንዲሁም መደበኛ የመወያያ መድረክ የተዘረጋ እና ተግባራዊ የተደረገ መሆኑን መገምገም፤

የሚሉ ናቸው፡፡

የኦዲት የመመዘኛ መስፈርት

17. ከላይ የተለዩትን የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች ለመመዘን የሚረዱ 27 የኦዲት የመመዘኛ መስፈርቶች (Evaluative criteria) ተዘጋጅቶ ኤጀንሲው አስተያየት እንዲሰጥበት ተደርጓል፡፡ የኦዲት የመመዘኛ መስፈርቶችን ለማዘጋጀት መሰረት የሆኑት የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ኤጀንሲ ማቋቋሚያ አዋጅ፣ ስትራቴጂክ ዕቅድ፣ የተለያዩ መመሪያዎች፣ በኤጀንሲው የተጠናው የመሰረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ ጥናት ሰነድ፣ ውጤት ተኮር የምዘና ሰነድ እና መልካም ተሞክሮዎች ናቸው፡፡ የተዘጋጁት መመዘኛ መስፈርቶች ከዚህ ሪፖርት ጋር አባሪ 2 ተያይዘዋል፡፡

የኦዲቱ ወሰንና ዘዴ

18. ኦዲቱ የተከናወነው በኢትዮጵያ ክዋኔ ኦዲት ደረጃዎች (Ethiopian Performance Audit Standards) እና ለመስሪያ ቤታችን በአዋጅ ቁጥር 669/2002 በተሰጠው ስልጣን መሰረት ነው፡፡ ዝርዝር ኦዲቱ የሸፈነው ከ2002-2005 ያሉትን የአራት በጀት ዓመታት የሥራ ክንውኖች ነው፡፡

19. ዝርዝር ኦዲቱ በዋነኛነት የተከናወነው በበጎ አድራጎት ድርጅቶች እና ማኅበራት ኤጀንሲ ዋና መ/ቤት ሲሆን፣ የ40 በጎ አድራጎት ድርጅቶችን ፋይል በመከለስ፤ ከነዚህ ውስጥ በአዲስ አበባ፣ በድሬዳዋ እና በሐረሪ የሚገኙ 10 የበጎ አድራጎት ድርጅቶችን በአካል ተገኝቶ በመጎብኘት፣ ለኃላፊዎቻቸው ቃለ-መጠይቅ በማቅረብ እና ለ5 የፌዴራል ዘርፍ አስተዳዳሪዎችና ለ12

የክልል የዘርፍ አስፈፃሚዎች ለሚመለከታቸው ኃላፊዎች ቃለ-መጠይቅ በማቅረብና ከኦዲት አቅጣጫው ጋር ተያያዥ የሆኑ መረጃዎችን በመከለስ ነው፡፡ በዝርዝር ኦዲቱ የታዩ የፌደራል ዘርፍ አስተዳዳሪዎች፣ የክልል ዘርፍ አስፈፃሚዎች እና የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ዝርዝር በአባሪ 3 ተያይዟል፡፡

ክፍል ሁለት

የኦዲት ግኝቶች

I. የበጎ አድራጎት ድርጅቶች የፕሮጀክት አፈፃፀም፣ ክትትልና ቁጥጥር በተመለከተ የወጡ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎችን ማስፈፀም የሚያስችል የአሠራር ሥርዓት መዘርጋቱን እና ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ፤

የበጎ አድራጎት ድርጅቶችን የፕሮጀክት አፈፃፀምና ክትትል በተመለከተ፤

20. ኤጀንሲው በስትራቴጂክ እና በአመታዊ ዕቅዱ መሰረት የበጎ አድራጎት ድርጀቶችን የመስክና የዴስክ ክትትል ሊያደርግ ይገባል፡፡ እንዲሁም ለኤጀንሲው እና ለዘርፍ አስተዳዳሪዎች የእያንዳንዱን የበጀት ዓመት ዋና ዋና የስራ ክንዋኔዎችን እና የኦዲት ሪፖርት እንዲያቀርቡ ሊያደርግ ይገባል፡፡

21. ኤጀንሲው ባዘጋጀው የስትራቴጂክ እና አመታዊ ዕቅድ መሰረት የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ላይ በመደበኛነት የመስክ እና የዴስክ (በኤጀንሲው የተመዘገቡ በጎ አድራጎት ድርጅቶችን ማህደራቸውን በመመርመር) ክትትል ባለመደረጉ በኦዲቱ ወቅት የቀረቡት የሶስት በጀት አመታት የእቅድ አፈፃፀም ሪፖርቶች ሲክለሱ፡- የሚከተለት ሁኔታዎች ታይተዋል፡፡

22. የመስክ ክትትል ግምገማን በተመለከተ፡-

- በ2003 በጀት አመት 300 የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማኅበራትን የመስክ ክትትል በማድረግ የስራ እንቅስቃሴያቸውን ለመገምገም አቅዶ 118 ድርጅቶችንና ማኅበራትን (39.3%) ብቻ ክትትል ማድረጉን፣
- በ2004 በጀት ዓመት 600 በጎ አድራጎት ድርጅቶችንና ማኅበራትን የመስክ ክትትል በማድረግ የስራ እንቅስቃሴያቸውን ለመገምገም ቢያቅድም በዓመቱ መጨረሻ 176 (29.3%) ድርጅቶች ላይ ብቻ ክትትል ማድረጉን፣
- በ2005 በጀት አመት 300 የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራትን የመስክ ክትትል ለማድረግ አቅዶ የ176 (59%) ክትትል መደረጉ፣

የተገለፀ ቢሆንም በናሙና በተመረጡት በጎ አድራጎት ድርጅቶች ላይ የተደረጉ የመስክ ክትትል ሪፖርቶች ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ እንዲቀርቡ ተጠይቆ ሊቀርቡ አልቻሉም፡፡

23. የዴክስ ክትትል (የበጎ አድራጎት ድርጅቶችን ማህደር መመርመርን) በተመለከተ፡-

- በ2004 በጀት ዓመት 2060 በጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማኅበራትን የዴስክ ክትትል ለማድረግ አቅዶ 1549 (75%) መደረጉን፣
- ከላይ ከተገለፁት የዴክስ ክትትል ከተደረገባቸው 1549 ድርጅቶችና ማህበራት ውስጥ 839ኙ (54%) የኦዲት ሪፖርት ያላቀረቡ ሲሆን 833ቱ (53.8%) ደግሞ ዓመታዊ የስራ ክንውን ሪፖርት ያላቀረቡ መሆኑ፣
- በ2005 በጀት ዓመት 2711 በጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ላይ የዴስክ ክትትል ለማድረግ ታቅዶ 2471 (91%) መደረጉን፣

በኦዲቱ ወቅት ለመረዳት ተችሏል፡፡

24. ከየዘርፉ አስተዳዳሪዎች (የየሴክተሩ ሚኒስቴር መ/ቤቶች) ጋር የፕሮጀክት ስምምነት ያደረጉ በጎ አድራጎት ድርጅቶች የእቅድና የእቅድ ክንውን ሪፖርት በመደበኛነት ለዘርፍ አስተዳዳሪዎቹ የማያቀርቡ መሆኑን፣ በዚህም ምክንያት በድርጅቶቹ ላይ የተወሰደ የማስተካከያ እርምጃ አለመኖሩ ታውቋል፡፡

25. በተጨማሪም በኦዲቱ ወቅት በናሙና የመስክ ምልከታ ከተደረገባቸው 10 በጎ አድራጎት ድርጅቶች ውስጥ 8ቱ በሶስቱም በጀት ዓመታት በኤጀንሲው የመስክ ክትትል ያልተደረገባቸው መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

26. ስለሁኔታው የኤጀንሲው የክትትልና ድጋፍ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ተጠይቀው በሰጡት መልስ ለሥራው የተቀጠሩት ሰራተኞች በስራ ላይ የመቆየት ችግር መኖሩ እና አዲስ የተቀጠሩትም ስልጠና ወስደው ወደ ስራ እስኪገቡ ድረስ በተፈጠረው የጊዜ ክፍተት ምክንያት አፈፃፀሙ ዝቅተኛ መሆኑን እና የክትትል ሪፖርቶችም በያንዳንዱ የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ፋይል ውስጥ የሚቀመጥ በመሆኑ ከፋይሉ ውስጥ እየወጣ መታየት የሚችል መሆኑን ገልጸዋል፡፡

27. የሥራ ኃላፊው ይህንን ይበሉ እንጂ በናሙና ተመርጠው በታዩት 40 የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ፋይል ውስጥ የመስክ የክትትል ሪፖርቱ ሊገኝ አልቻለም፡፡

28. ይህ በመሆኑ ኤጀንሲው፣ የዘርፍ አስተዳዳሪዎች እና የክልል አስፈጻሚ አካላት የበጎ አድራጎት ድርጅቶችን በገቡት የፕሮጀክት ውል መሰረት በየወቅቱ ለመከታተል፣ ለመቆጣጠርና ተገቢውን የእርምት እርምጃ እንዳይወስዱ ከማድረጉም በላይ፣ የመንግስትን ክፍተት (gap) ይሞላሉ ተብሎ የታመነባቸው በጎ አድራጎት ድርጅቶች በአግባቡ እና በህግ መሰረት ለህብረተሰቡ (ለተጠቃሚዎች) አገልግሎት እየሰጡ መሆኑን ለማረጋገጥ አያስችልም፡፡

ኤጀንሲው በዴስክና በመስክ ላደረጋቸው የክትትል ሪፖርቶች ግብረ መልስ መስጠቱን በተመለከተ

29. ኤጀንሲው በሚያዘጋጀው አመታዊ የእቅድ ክንውን ሪፖርት ውስጥ በበጎ አድራጎት ድርጅቶች የፕሮጀክት አፈፃፀም ላይ የታዩ ክፍተቶች እና የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎችን ሊያካትት ይገባል፡፡ እንዲሁም በኤጀንሲው የዴስክና የመስክ ክትትል በታዩ ችግሮች ላይ በጎ አድራጎት ድርጅቶች የማስተካከያ እርምጃ እንዲወስዱ መደረግ አለበት፡፡

30. በኦዲቱ ወቅት በአካል ከታዩት 10 በጎ አድራጎት ድርጅቶች ውስጥ ሁለቱ በመስክ ክትትል የተደረገላቸው መሆኑን እና በቃል አስተያየት የተሰጣቸው መሆኑን ሲገልፁ 8ቱ ክትትል ያልተደረገባቸው መሆኑን፣ አንዲሁም ኤጀንሲው በዴስክና በመስክ ክትትል ለታዩ ችግሮች የማስተካከያ ግብረመልስ ሪፖርት ለድርጅቶቹ ስለመስጠቱ ለኦዲት ቡድኑ ማስረጃ አላቀረቡም፡፡

31. በሌላ በኩል የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳደር ፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ በተለያዩ ጊዜያት የአሰራር ክፍተት በታየባቸው የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ላይ ኤጀንሲው ህጋዊ እርምጃ እንዲወስድ እና በድርጅቶቹ እጅ ያለውና በህዝብ ስም የተሰበሰበው ሀብትና ንብረት ብክነት እንዳይደርስበት በማለት ለኤጀንሲው በተለያየ ጊዜ በተፃፉ በደብዳቤዎች ቢያሳውቅም በድርጅቶቹ ላይ ስለተወሰደው እርምጃ ወይም ስለተሰጠው የመፍትሄ ሀሳብ ለቢሮው እንዳልተገለፀለት ለቢሮው ኃላፊዎች ከተደረገ ቃለ መጠይቅና ከተከለሱ የኦዲት ማስረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

32. ስለሁኔታው የኤጀንሲው የክትትልና ድጋፍ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ተጠይቀው በሰጡት መልስ ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ጋር በጋራ መድረኮች የተወያዩ መሆናቸውን ነገር ግን በደብዳቤ የተሰጣቸው መልስ የሌለ መሆኑን ገልፀዋል፡፡ የአዲስ አበባ መስተዳድር ፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ግን የመጨረሻ ውሳኔ መስጠት የኤጀንሲው ኃላፊነት ሆኖ ሳለ ምንም ውሳኔ ሳይሰጥ እና ችግሮቹ ሳይቀረፉ መቅረቱን የገለጸ በመሆኑ የተሰጠውን መልስ አልተቀበልነውም፡፡

33. ይህም በመሆኑ በጎ አድራጎት ድርጅቶች ያሉባቸውን ክፍተቶችና ችግሮች በየጊዜው እንዲያስተካክሉ አለመደረጉና ከክልል አስፈፃሚ አካላትም በበጎ አድራጎት ድርጅቶች ላይ የተገኙትን ችግሮች አጣርተው ኤጀንሲው እርምጃ እንዲወስድ ሲያሳውቁ እርምጃ

አለመወሰዱ በሕዝብ ስም ተሰብስቦ የመጣው ገንዘብና ሀብት ለተባለለት ዓላማ ሥራ ላይ መዋሉን ማረጋገጥ አዳጋች ያደርገዋል፡፡

የበጎ አድራጎት ድርጅቶች የዓላማ ማስፈፀሚያና አስተዳደራዊ ወጭ በመመሪያው መሰረት መፈፀሙን በተመለከተ፣

34. ኤጀንሲው ማንኛውም የበጎ አድራጎት ድርጅት በየበጀት ዓመቱ ከሚያወጣው ወጭ ከ70 በመቶ የማያንሰውን ለዓላማ ማስፈፀሚያና ከ30 በመቶ የማይበልጠውን ለአስተዳደራዊ ወጭ ማዋላቸውን፣ መመሪያውን ጠብቀው መስራታቸውን ሊከታተልና ሊገመግም ይገባል፡፡ ይህንንም ተላልፈው በተገኙ በጎ አድራጎት ድርጅቶች ወይንም ማህበራት ላይ በህጉ መሰረት እርምጃ ሊወስድ ይገባል፡፡

35. ኤጀንሲው በ2004 በጀት ዓመት በዴስክ ክትትል ካደረገባቸው 1549 በጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማኅበራት መካከል 1250 (81%) እንዲሁም በ2005 በጀት ዓመት ፋይላቸው ከተመረመረው 2471 በጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማሕበራት መካከል 882 (36%) ለአስተዳደራዊ ወጭ ከ30 በመቶ በላይ የተጠቀሙ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

36. በተጨማሪ በመስክ ኦዲት ወቅት በናሙና ከታዩትና ከአገር ውስጥ ገቢ ከሰበሰቡ ሶስት ድርጅቶች ውስጥ፣

- ማሪስቶፕስ ኢንተርናሽናል እ.ኤ.አ በ2011 እና በ2012 (እንደ ኢትዩጵያውያን አቆጣጠር በ2004 እና በ2005 ዓ.ም) ድርጅቱ ባቀረበው የኦዲት ሪፖርት ላይ ለአስተዳደራዊ ወጪ 36 በመቶ የተጠቀመ መሆኑ ባቀረበው ሪፖርት የተጠቀሰ ቢሆንም በኦዲቱ ወቅት በተሰራው ትንተና መሰረት ከአገር ውስጥ የሚሰበስበው ገቢ በመመሪያው መሰረት ለአላማ ማስፈፀሚያ ብቻ መዋል ያለበትን ለአስተዳደራዊ ወጪ የተጠቀሙ በመሆኑ ከዕርዳታ ካገኙት ገንዘብ ጋር ተደምሮ በአጠቃላይ ለአስተዳደራዊ ወጪ ያዋሉት በሁለቱ በጀት አመታት እ.ኤ.አ በ2011 እና በ2012 (2004 እና 2005 ዓ.ም) 47 በመቶ እና 44 በመቶ መሆኑ፤

- ኪውር ኢንተርናሽናል የተባለው በጎ አድራጎት ድርጅት እ.ኤ.አ በ2012 (2005 ዓ.ም) ባቀረበው የሂሳብ ሪፖርቱ ለአስተዳደራዊ ወጪ ከ30 በመቶ በታች 25 በመቶ እንደተጠቀመ ሪፖርት ያደረገ ቢሆንም በኦዲቱ ወቅት በተሰራው ትንተና መሰረት ከአገር ውስጥ የሚሰበስበው ገቢ በመመሪያው መሰረት ለአላማ ማስፈፀሚያ ብቻ መዋል ያለበትን ለአስተዳደራዊ ወጪ የተጠቀሙ በመሆኑ ከዕርዳታ ካገኙት ገንዘብ ጋር ተደምሮ በአጠቃላይ ለአስተዳደራዊ ወጪ ያዋሉት በ2012 (2005 ዓ.ም) 37 በመቶ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ዝርዝሩ በአባሪ 6 ተያይዟል፡፡

37. በተጨማሪም በ2003 በጀት አመት በዴክስ ክትትል ከታዩ 1210 በጎ አድራጎት ድርጅቶች ውስጥ 412(34%)፣ በ2004 በጀት አመት በዴክስ ክትትል ከታዩ 1549 ውስጥ 839(54%)፣ በ2005 በጀት አመት በዴክስ ክትትል ከታዩ 2471 ውስጥ 304 (12%) የኦዲት ሪፖርት ያላቀረቡ መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ መረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

38. መመሪያን ጠብቀው በማይሰሩ ድርጅቶች ወይም በየበጀት ዓመቱ የአስተዳደር ወጭ ከ30 በመቶ በላይ፣ የዓላማ ማስፈጸሚያ ከ70 በመቶ በታች የሀብት አጠቃቀም ባሳዩ ድርጅቶች ላይ ከብር 5,000-100,000 (ከአምስት ሺ እስከ አንድ መቶ ሺህ ብር) ድረስ እንደሚቀጡ ኤጀንሲው ታህሳስ 2003 ዓ.ም ባወጣው የክትትልና ድጋፍ ስራ መመሪያ (ጋይድ ላይን) ቢያስቀምጥም ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ ይህን አይነት እርምጃ የተወሰደበት በጎ አድራጎት ድርጅት አለመኖሩ ታውቋል፡፡ እንዲሁም ኤጀንሲው መመሪያን ሳይጠብቁ የሚሰሩ ድርጅቶች ችግሩ ሳይፈታ ፈቃዳቸውን በማደስ ወደስራ እንዲገቡ ያደረገ መሆኑ ታውቋል፡፡

39. በኦዲት ወቅት በአካል ለታዩ 10 በጎ አድራጎት ድርጅቶች ለቀረበ ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ በዓላማ ማስፈፀሚያና አስተዳደራዊ ወጭ ክፍፍል ዙሪያ ችግሮች እንዳሉ፤ የትኛው ወጭ በየትኛው መደብ መመደብ እንዳለበት የጠራ ግንዛቤ እንደሌላቸው፣ በመመሪያውም ላይ በዝርዝር ተገልፆ አለመቀመጡን፣ የድርጅቶቹን ነባራዊ የስራ ሁኔታ ያገናዘበ አለመሆኑን፣ እና መመሪያዎቹ ሲወጡም ኤጀንሲው በጎ አድራጎት ድርጅቶች ተወያይተው አስተያየት እንዲሰጡበት ያልተደረገ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

40. ስለጉዳዩ የኤጀንሲው የክትትል እና ድጋፍ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ተጠይቀው በሰጡት መልስ በመመሪያው ዙሪያ ከድርጅቶቹ ጋር በቀጥታ የተወያዩት መመሪያው ከወጣ በኋላ ቢሆንም የድርጅቶቹን የተወሰኑ አስተያየቶች ወስደው መመሪያዎቹን ያሻሻሉበት ሁኔታ መኖሩን እንዲሁም መመሪያው ስራ ላይ ከዋለ 17 ወራቶች በመሆኑ መመሪያውን ጠበቅ አድርጎ መተርጎም ስለማያዋጣቸው ህጉን ተከተልው አለመስራታቸውንና ወደፊት እንዲያስተካክሉ በፅሁፍ እየጠየቁ ኃላፊነቱን እንዲወስዱ ማድረጉ ገንቢ አስተዳደራዊ እርምጃ ወይም መፍትሄ ተብሎ በመወሰዱ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

41. በመሆኑም በመመሪያው መሰረት ለዕርዳታው ከተመደበው ገንዘብ ለአላማ ማስፈፀሚያ 70 በመቶ እና የአስተዳደራዊ ወጭ ማስፈጸሚያ ደግሞ 30 በመቶ በመመደብና በዚሁ

መሰረት ወጪ በማድረግ የማይሰሩ በጎ አድራጎት ድርጅቶች በመኖራቸው በህዝብ ስም የመጣን ገንዘብ ላልተፈቀደ አላማ ለማዋል ክፍተት የሚፈጥር እና ኤጀንሲው በአዋጅ የተሰጠውን ስልጣንና ኃላፊነት ተግባራዊ እንዳያደርግ ያደርገዋል፡፡

የበጎ አድራጎት ድርጅቶች የዓላማ ማስፈፀሚያና የአስተዳደራዊ ወጪን ለማስፈፀም የወጣውን ክፍፍል በተመለከተ

42. ኤጀንሲው የበጎ አድራጎት ድርጅቶችን የዓላማ ማስፈፀሚያና አስተዳደራዊ ወጪን በአዋጁ መሰረት ተግባራዊ የሚሆንበት የአፈጻጸም መመሪያ አዘጋጅቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ የአፈጻጸም መመሪያውም የትኛው ወጪ ለአስተዳደራዊ ተግባር (30%) እና የትኛው ወጪ አላማ ማስፈፀሚያ (70%) እንደሆነ የሚገልፅ እና ለአፈጻጸምም ለክትትል በሚመች መልኩ ሊዘጋጅ ይገባል፡፡ የተጋጀውን ዝርዝር መመሪያም ለበጎ አድራጎት ድርጅቶቹ በማሳወቅ ተግባራዊ ማድረጋቸውን ሊከታተል ይገባል፡፡

43. ኤጀንሲው የዓላማ ማስፈፀሚያና አስተዳደራዊ ወጪን ለይቶ የሚያሳይ መመሪያ ያዘጋጀ መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡ መመሪውንም ለመተግበር በአገሪቱ የሚሰሩ በጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራትን በአስር ክፍፍል (cluster) መድቧቸዋል፡፡ ነገር ግን በኦዲቱ ወቅት በናሙና ከታዩ በጎ አድራጎት ድርጅቶች ውስጥ በአቅም ግንባታና በምርምር ስራ የተሰማሩ ድርጅቶች በክፍፍሉ ውስጥ እንዳልተመደቡ ታውቋል፡፡

44. በኦዲቱ ወቅት መጠይቅ የቀረበላቸው ከቡና ጋር በተያያዘ የአቅም ግንባታ ለመስራት ፈቃድ የወሰደው የቴክኖሰርቭ ኢንክ የተባለ የበጎ አድራጎት ድርጅት ኃላፊዎች እንደገለፁት ድርጅቱ የሚሰራው የአቅም ግንባታና ድጋፍ ላይ ሲሆን የድርጅቱን ስራ (እንቅስቃሴ) ያገናዘበ የአስተዳደራዊና የአላማ ማስፈፀሚያ ወጪ ክፍፍል ባለመኖሩ ከኤጀንሲው ጋር አለመግባባት እንደተፈጠረና ሥራቸው ላይ ተጽዕኖ ማሳደሩን ገልፀዋል፡፡

45. ስለሁኔታው የኤጀንሲው የክትትልና ድጋፍ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ተጠይቀው በሰጡት መልስ መመሪያውን ለመተግበር የሚያስቸግሩ መሆናቸው የታመነባቸው የተወሰኑ ወጭዎችን በአላማ ማስፈፀሚያ በማካተት ያሻሻሉ ቢሆንም ጥያቄ ላቀረበ ሁሉ ግን የማሻሻል ዓላማ የሌላቸው መሆኑን ገልፀዋል፡፡ ሆኖም የአቅም ግንባታና የምርምር ሥራ ላይ የሚሰማሩ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች በክፍፍሉ ለምን እንዳልተካተቱ ምላሽ አልሰጡም፡፡

46. በመሆኑም በአቅም ግንባታ እና በምርምር ስራ የተሰማሩ በጎ አድራጎት ድርጅቶች መመሪያውን እንዳይተገበሩ ከማድረጉም በላይ ኤጀንሲው ፈቃድ የሰጣቸውን ድርጅቶችን ወጥ በሆነ አሰራር ማስተዳደር እንዳይችል ያደርገዋል፡፡

ኤጀንሲው ለገቢ ማስገኛ እና ለህዝባዊ መዋጮ ፈቃድ የሰጣቸውን በጎ አድራጎት ድርጅቶች በተመለከተ

47. በጎ አድራጎት ድርጅቶች ገቢ ማስገኛ ሥራ ላይ ለመሰማራት ከኤጀንሲው ፈቃድ ሊያገኙና እና ከሚመለከተው የመንግስት አካል የንግድ ፈቃድ ሊያወጡ ይገባል፡፡ ከገቢ ማስገኛ የሚገኘውን ገንዘብ እንቅስቃሴ ከበጎ አድራጎት ስራው የተለየ የሂሳብ መዝገብ ሊይዙ ይገባል፡፡ ከህዝብ በተለያየ መንገድ መዋጮ የሚሰበስቡ በጎ አድራት ድርጅቶች መዋጮ የሚሰበሰብቡበትን ዕቅድና የጊዜ ሰሌዳ በማቅረብ ከኤጀንሲው ፈቃድ መውሰድ አለባቸው፡፡ የሕዝባዊ መዋጮ የማሰባሰቢያ ጊዜ በተጠናቀቀ በ3 ወር ጊዜ ውስጥ ከመዋጮው ጋር የተያያዘ ማንኛውንም የገንዘብ እንቅስቃሴና የሀብት ሁኔታ የሚያሳይ ሪፖርት ማቅረብ አለባቸው፡፡ በገቢ ማስገኛ እና በሕዝባዊ መዋጮ የተሰበሰበው ገቢ ለዓላማ ማስፈፀሚያ ብቻ መዋሉ ሊረጋገጥ ይገባል፡፡

48. ኤጀንሲው በገቢ ማስገኛ ስራ ላይ መሰማራት ለሚፈልጉ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ጥያቄ ሲያቀርቡ እየመረመረ ፈቃድ የሚሰጥ መሆኑ ታውቋል፡፡ ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት፡-

- ኤጀንሲው በ2004 በጀት አመት ለ34፣ በ2005 በጀት አመት ለ34 በጠቅላላው ለ68 በጎ አድራጎት ድርጅቶች ገቢ ማስገኛ ስራ ላይ እንዲሰማሩ ፈቃድ የሰጠ ቢሆንም ፈቃድ የሰጣቸው ድርጅቶች (Income generating actitvity, IGA) በመመሪያው መሰረት መስራታቸውንና በአመቱ መጨረሻ የተለየ ሂሳብና የኦዲት ሪፖርት ማቅረባቸውን ክትትል አለማድረጉ፣
- የገቢ ማስገኛ ፍቃድ በገቢ ማስገኛ ሥራ (በIncome generating actitvity) በመመሪያው መሰረት የማይካተቱ ነገር ግን በወጪ መጋራት (cost sharing) እያስከፈሉ የጤና አገልግሎት የሚሰጡ በጎ አድራጎት ድርጅቶች የሚመሩበት ግልፅና ወጥ የሆነ መመሪያ ያልተዘጋጀ መሆኑ፤
- በ2004 በጀት አመት ለ23 እና በ2005 በጀት አመት ለ26 በጠቅላላው ለ49 በጎ አድራጎት ድርጅቶች የሕዝባዊ መዋጮ ፈቃድ የሰጠ ቢሆንም መዋጮውን ባከናወኑ በ3ወር ጊዜ ውስጥ ዝርዝር ሪፖርት ማቅረባቸውን የማይከታተል እና

- ከሕዝባዊ መዋጮ የሰበሰቡትን ገንዘብ ለዓላማ ማስፈፀሚያ ብቻ መዋሉ የማይሰላ እና የማይረጋገጥ መሆኑ፣

በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡

49. የኤጀንሲው ኃላፊዎች ስለሁኔታው ተጠይቀው በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ (fact sheet) ላይ በሰጡት አስተያየት የወጪ መጋራት መመሪያ ማውጣት የኤጀንሲው ኃላፊነት እንደሆነ ነገር ግን የመመሪያ ረቂቅ እየተዘጋጀ መሆኑን እና በባለሙያዎች መጓደል እንደዘገየ፣ በገቢ ማስገኛ ሥራ (Income generating actitvity) መመሪያውን ጠብቀው መስራታቸውን በመስክ ክትትል የሚታዩ መሆኑን ነገር ግን እስካሁን በክትትል በደረሱባቸው ድርጅቶች ላይም እርምጃ እንዳልወሰዱ ገልፀዋል፡፡

50. በመሆኑም ገቢ የሚሰበስቡ በጎ አድራጎት ድርጅቶች ላይ ክትትል ባለመደረጉ፣ የንግድ ፈቃድ ሳያወጡ ገንዘብ እያስከፈሉ አገልግሎት የሚሰጡ ድርጅቶች በመኖራቸው እና ከህዝብ በመዋጮም ሆነ ከአገልግሎት ክፍያ የሚሰበሰበው ገንዘብ ለተፈቀደበት አላማ መዋሉን ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡ የወጪ መጋራት መመሪያ ባለመውጣቱ ምክንያት ድርጅቶቹ የሚያስከፍሉት ዋጋ የህብረተሰቡን የመክፈል አቅም እና ከፕሮጀክቱ ዘላቂነት (sustainability) አንፃር ማገናዘብ ስለማይቻል ለብልሹ አሰራር በር ይከፍታል፡፡

ከውጭ ምንጭ ከ10 በመቶ በላይ ገቢ ማግኘት ስለማይችሉ የኢትዮጵያ በጎ አድራጎት ድርጅቶች በተመለከተ

51. ኤጀንሲው የኢትዮጵያ በጎ አድራጎት ድርጅቶች ህጉ በሚፈቅድላቸው መሰረት የገቢ ምንጫቸውን 90 በመቶ ከሃገር ውስጥ ምንጭ እና ከ10 በመቶ የማይበልጥ ከውጭ የማምጣት ህጉን አክብረው መስራታቸውን መከታተል እና እርምጃ መውሰድ አለበት፡፡

52. በኦዲቱ ወቅት ኤጀንሲው በ2004 በጀት ዓመት 60 እንዲሁም በ2005 በጀት ዓመት 59 በኢትዮጵያ በጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማኅበራት ስም ፈቃድ የወሰዱ ከ10 በመቶ በላይ የገቢ ምንጭ ከውጭ ያገኙ መሆናቸው በዴስክ ክትትል ሲደርግ ያገኘ ቢሆንም ምንም አይነት እርምጃ እንዳልወሰደ ታውቋል፡፡

53. የኤጀንሲው ኃላፊዎች ስለሁኔታው ተጠይቀው በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ (fact sheet) ላይ በሰጡት አስተያየት ህጉን ጠብቀው መሄድ ያለባቸው በመሆኑ ከ10 በመቶ በላይ ከውጭ ምንጭ አምጥተው የተገኙት ላይ በሥራ እየቀጠሉ ማስተካከል እንደሚሻል ታምኖበት ድርጅቶቹን እንዲያስተካክሉ ተነግሯቸዋል ብለዋል፡፡ ኃላፊዎቹ ይህን ይበሉ እንጂ ኤጀንሲው ማስተካከያ እንዲያደርጉ ስለማድረጉ ማስረጃ አልቀረበም፡፡

54. ይህም የሚያሳየው ኤጀንሲው በህጉ መሰረት ከ10 በመቶ በላይ የገቢ ምንጭ ከውጭ ማምጣት የማይችሉ የኢትዮጵያ በጎ አድራጎት ድርጅቶች አምጥተው ሲገኙ ተገቢውን ክትትል እና አስተማሪ የሆነ እርምጃ አለመውሰዱ ድርጅቶቹ በህግ ከተፈቀደላቸው ተግባር ውጭ እንዲሰማሩ በር ይከፍታል፡፡

በጎ አድራጎት ድርጅቶች የፕሮጀክት ፕሮፖዛል ግምገማን በተመለከተ

55. ኤጀንሲው በየዘርፉ የሚላኩ የፕሮጀክት ፕሮፖዛሎችን ለመገምገም የሚያስችል ወጥ የሆነ ማንዋል ወይም የአሰራር ስርዓት እና የሚገመግሙ ሙያተኞች በመመደብ አገልግሎቱን በአንድ መስኮት ስር ሊሰጥ ይገባል፡፡

56. ኤጀንሲው ከ2003-2007 ባወጣው ስትራቴጂክ እቅድ እና በየዓመቱ ባወጣቸው እቅዶች የፕሮጀክት ፕሮፖዛል ግምገማ በኤጀንሲው ሁለገብ የምዝገባ ባለሙያ፣ የዘርፍ አስተዳዳሪዎች ፕሮጀክት ገምጋሚ ባለሙያዎችን በኤጀንሲው እንዲመድቡ በማድረግ፣ እንዲሁም ፕሮጀክትን ለመገምገም የሚያስችል ወጥ ማንዋል ከዘርፍ አስተዳዳሪዎች ጋር በጋራ በማዘጋጀት የኤጀንሲውን የምዝገባ ኦፊሰሮች በማሰልጠን ደንበኛ ተኮር በሆነ መልኩ አገልግሎቱን በአንድ መስኮት ስር ለመስጠት ያቀደ ቢሆንም ተግባራዊ ያልተደረገ መሆኑን ለመረዳት ተችሏል፡፡

57. በኦዲቱ ወቅት በናሙና ከታዩ አምስት የዘርፍ አስተዳዳሪ ሚኒስቴር መ/ቤቶች መካከል በሶስቱ (ሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚ/ር፣ ትምህርት ሚ/ር፣ እና የሴቶች፣ ህጻናትና ወጣቶች ጉዳይ ሚ/ር) የበጎ አድራጎት ድርጅቶችን ፕሮጀክት ፕሮፖዛል የሚገመግምና የፕሮጀክት አፈፃፀም ክትትል የሚያደርግ ራሱን የቻለ ክፍል የሌለ ሲሆን ይህ ሥራ ከሌሎች ሥራዎች ጋር ተደርቦ እንደሚሰራ ለመስሪያ ቤቶቹ ኃላፊዎች ከቀረበ ቃለ-መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡

58. በናሙና በታዩ የክልል የዘርፍ አስፈፃሚ አካላት እና ውክልና በተሰጣቸው የክልል ቢሮዎች ከቀረበ ቃለ-መጠይቅ ለመረዳት እንደተቻለው ውክልና በተሰጣቸው የክልል ቢሮዎች ከሀረሪ ክልል በስተቀር በሌሎች ክልሎች/አስተዳደሮች (አዲስ አበባ፣ ኦሮሚያ፣ እና ድሬዳዋ) ራሱን የቻለ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች የፕሮጀክት ፕሮፖዛል የሚገመግም ክፍል የተቋቋመ ቢሆንም በዘርፍ አስፈፃሚ መ/ቤቶች ግን ከድሬዳዋ ሴቶች፣ ህፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ቢሮ በስተቀር በሌሎች የክልል ቢሮዎች (በድሬዳዋ አስተዳደር ጤና ቢሮ፣ በኦሮሚያ ክልል ጤና ቢሮ፣ በኦሮሚያ ክልል ግብርና ቢሮ ፣ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ጤና ቢሮ፣ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሴቶች፣ ህፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ቢሮ) ስራው በሌሎች ክፍሎች ተደርቦ እንደሚሰራ ታውቋል፡፡

59. ይህም በመሆኑ ለግምገማ ወደ ዘርፍ አስተዳዳሪዎች የሚላኩ የፕሮጀክት ፕሮፖዛሎች ኤጀንሲው በአንድ ቀን ውስጥ ገምግመው እንዲልኩ የሚልክላቸው ቢሆንም በተለያየ ምክንያት እስከ አንድ ወር የሚዘገይ መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡

የበጎ አድራጎት ድርጅቶች የፕሮጀክት አፈፃፀም ለመከታተል የሚያስችል መመሪያ መኖሩን በተመለከተ፣

60. ኤጀንሲው፣ የዘርፍ አስተዳዳሪዎች እና ክልል አስፈፃሚዎች የፕሮጀክት ስምምነት ተፈራርመው ወደ ትግበራ የገቡ በጎ አድራጎት ድርጅቶችን የፕሮጀክት አፈፃፀም ለመከታተል የሚያስችል መመሪያ ሊያዘጋጅና ለየድርጅቶቹ ሊያሰራጭ ይገባል፡፡

61. በኦዲቱ ወቅት በናሙና ከታዩት አምስት የዘርፍ አስተዳዳሪ ሚኒስቴር መ/ቤቶች አራቱ (ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር፣ የትምህርት ሚኒስቴር፣ የሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር እና የግብርና ሚኒስቴር) እንዲሁም በናሙና ከታዩ አራት የክልል የዘርፍ አስፈፃሚ አካላት መካከል በድሬዳዋ አስተዳደርና እና በሀረሪ ክልል የበጎ አድራጎት ድርጅቶችን ፕሮጀክት ፕሮፖዛል ለመገምገም የሚያስችል ወጥ የሆነ መመሪያም ሆነ ቼክ ሊስት ያልተዘጋጀ መሆኑ ታውቋል፡፡

62. የዘርፍ አስተዳዳሪዎች በፕሮጀክት ስምምነት መሰረት የበጎ አድራጎት ድርጅቶችን የአመቱን የአጋማሽ ግምገማ (Midterm evaluation) እንደማያከናውኑ፣ የመጨረሻ የግምገማ ሪፖርት(Terminal evaluation) ሲያከናውኑ የገምጋሚዎቹ (የክልል አስፈፃሚ አካላት ሠራተኞች) የትራንስፖርትና አበል ወጪ የሚሸፈነው በተገምጋሚዎቹ (በበጎ አድራጎት ድርጅቶች) በመሆኑ ይህም የግምገማ ሪፖርቱ ላይ አሉታዊ ተፅእኖ ሊያሳድር እንደሚችል በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡

63. በሀረሪ ክልል ውስጥ በሚገኙ 10 የህፃናት ማሳደጊያ ድርጅቶች በተደረገ የግምገማ ሪፖርት የተለያዩ ድርጅቶች በግቢያቸው ውስጥ ክሊኒክና የህክምና ባለሙያ የሌላቸው መሆኑ፣ ለህፃናት የተሟላ መዝናኛና መጫወቻ ስፍራ የሌለ መሆኑ፣ በየድርጅቱ ውስጥ የሚገኙ ህፃናት መረጃ በተሟላ መልኩ ያልተያዘ፣ ድርጅቶች ህፃናትን ተቀብለው ሌሎች አማራጮችን ሳይጠቀሙ በጉዲፈቻ እንደሚልኩ፣ ከክልሉ ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ወይም ከሚመለከተው አካል ጋር የሥራ ስምምነት የሌላቸውና ፈቃድም ያልተሰጣቸው፣ አድራሻቸው ሊታወቁ ያልቻሉ ድርጅቶች መኖራቸውን በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ መረጃዎች ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

64. የሴቶች፣ ህፃናትና ወጣቶች ሚኒስቴር የፕሮጀክት ስምምነት ከበጎ አድራጎት ድርጅቶች ጋር የማይፈራረሙ በመሆኑ ከአንድ ክልል በላይ የሚሰሩ ድርጅቶች ከየክልሎች ጋር ለመፈራረም የተገደዱ መሆኑን፣ በሚኒስቴር መ/ቤቱ የህፃናት ጉዳይ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር በጉዲፈቻ ላይ የሚሰሩ ድርጅቶች ጋር ብቻ የሚፈራረሙ ሲሆን እስከ 2004 ዓ.ም ድረስ ክትትል ተደርጎባቸው የማያውቅ መሆኑ፣ እንዲሁም በሚኒስቴር መ/ቤቱ በታህሳስ 2005 ዓ.ም በአገሪቱ ያሉ 63 የጉዲፈቻ አገናኝ ኤጀንሲዎች የመመዘኛ መስፈርት አውጥተው ገምግመው ሪፖርት ያደረጉ ቢሆንም በሪፖርቱ ላይ በእያንዳንዱ ኤጀንሲ ምን ያህል ልጆች በጉዲፈቻ ወደተለያዩ አገራት እንደተላኩ፣ ከተላኩ ጊዜ ጀምሮ ያለ ታሪካቸው እና ያሉበት ሁኔታ ያልተገለፀ መሆኑ፤ በዚህም ምክንያት በጉዲፈቻ መልክ ከአገር የወጡ ልጆች በምን አይነት ሁኔታ እየኖሩ እንዳለ በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የማይታወቅ መሆኑ ታውቋል፡፡

65. የኤጀንሲው ኃላፊዎች ስለሁኔታው ተጠይቀው በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ (fact sheet) ላይ በሰጡት አስተያየት በሐረሪ ክልል ስለሚገኙት 10 የህፃናት ማሳደጊያ ድርጅቶች መቆጣጠርና ክትትል ማድረግ የክልሉ ሃላፊነት ሲሆን ኤጀንሲው መረጃ ሲደርሰው የራሱን ማጣሪያ እንደሚያደርግ ገልፀው ይህንን ጥቆማ እንደመነሻ ወስደው እንደሚከታተሉት ገልጸዋል፡፡

66. ከዚህ በተጨማሪም የኤጀንሲው ዋና ዳይሬክተር የመውጫ ስብሰባ ተደርጎ ሪፖርት ከደረሳቸው በኋላ ሌላ ስብሰባ በመ/ቤታችን እንዲመቻችላቸው ጠይቀው በዛ ወቅት በሰጡት መልስ በአዋጅ ቁጥር 621/2001 አንቀፅ 37 መሰረት የዘርፍ አስተዳዳሪዎች የበጎ አድራጎት ድርጅቶች በፕሮጀክት ስምምነታቸው መሰረት እየፈፀሙ መሆኑን የመከታተል፣ የመቆጣጠር እንዲሁም አስፈላጊውን እርምጃ የመውሰድ፤ የወሰደውን እርምጃ በ7ቀን ውስጥ ለኤጀንሲው የሚያሳውቅ በመሆኑ ኤጀንሲውን የማይመለከተውና የሚመለከታቸው የዘርፍ አስተዳሪዎች መሆናቸው ገልፀዋል፡፡

67. የኤጀንሲው ዋና ዳይሬክተር ይህን ቢሉም በአዋጅ ቁጥር 621/2001 በአንቀፅ 6 ላይ በጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ፈቃድ መስጠት፣ መመዝገብና መቆጣጠር የኤጀንሲው ሥልጣንና ተግባር መሆኑ ተገልጿል፡፡ መቆጣጠር ሲባል በጎ አድራጎት ድርጅቶች የሥራ እንቅስቃሴን በህጉ፣ በደንቡና የፕሮጀክት ስምምነቱ መሰረት በአግባቡ መስራታቸውን መከታተል ስለሆነ ይህ ተግባር ለኤጀንሲው የተከለከለ ተግባር መሆኑን በአዋጁ ላይ የማያመላክት በመሆኑ እንዲሁም ኤጀንሲው በአመታዊ ዕቅዱ ውስጥ በጎ አድራጎት ድርጅቶችን ለመከታተል ቢያቅድም ያልተገበረው መሆኑን ገልጸው በኦዲቱ ወቅት መልስ

የሰጡበት በመሆኑ በመጨረሻ ከኤጀንሲው ስራአስፈጻሚ የተሰጠው መልስ በኦዲቱ ወቅት ከተሰጠው ጋር የሚጣረስ በመሆኑ መልሱን ለመቀበል ያዳግታል፡፡

68. ኤጀንሲው በ2003 በጀት ዓመት የዘርፍ አስተዳዳሪዎች የበጎ አድራጎት ሥራን የሚገመግሙበትና እርምጃ የሚወስዱበት የአሰራር ማንዋል በማዘጋጀትና የምክክር መድረክ በማካሄድ ስራ ላይ ለማዋል አቅዶ ያላከናወነ መሆኑ ችግሮቹን ለመፍታት ያደረገው ጥረት በቂ አለመሆኑን አሳይቷል፡፡

በዳግም ምዝገባ ያልተመዘገቡ ድርጅቶችን በተመለከተ

69. ኤጀንሲው በዳግም ምዝገባ ያልተመዘገቡ በጎ አድራጎት ድርጅቶችንና ማኅበራትን አድራሻ በማፈላለግ ህጋዊ እርምጃ መውሰድ አለበት፡፡

70. ኤጀንሲው ከመቋቋሙ በፊት 3982 በጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማኅበራት ተመዝግበው የነበረ ሲሆን አዋጁ ከወጣ በኋላ በ2002 በዳግም ምዝገባ 1655 በጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማኅበራት ተመዝግበው ተገኝተዋል፡፡ ከቀሪዎቹ 2327 ድርጅቶችና ማኅበራት ውስጥ ዳግም ባልተመዘገቡ በጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማኅበራት አጣሪ ኮሚቴ ሲጣራ እስከ ሰኔ 2005 ድረስ

- 11 ድርጅቶች ቀደም ሲል በፍትህ ሚኒስቴር የተሰረዙ መሆናቸው፣
- 46 ድርጅቶች ዳግም ተመዝግበው የተገኙ መሆኑ፣
- 6 ድርጅቶች ንብረታቸው ተጣርቶ የሚፈለግባቸው ገንዘብ ከአምስቱ ድርጅቶች ብር 34,009.85 ወደ ዲፓዚት አካውንት ገቢ መደረጉ እና አንዱ ድርጅት የባንክ አካውንቱ የታገደበት መሆኑ፣
- 2 ማህበራት ተመሳሳይ አላማ ላለው ማህበር ንብረታቸው መተላለፉን፣
- 3 ድርጅቶች ዳግም አለመመዝገባቸው ተረጋግጦ ንብረት በማስረከብ ላይ የተገኙ መሆኑ የተጣራ ሲሆን፣
- የተቀሩት 2259 በጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማኅበራት አድራሻ በማፈላለግ ንብረታቸውን ያላጣራ፣ ፈቃዳቸውንም ያላስመለሰ እና ህጋዊ እርምጃ ያልወሰደ መሆኑ ታውቋል፡፡

71. ከዚህ በተጨማሪም በዳግም ምዝገባ ሳይመዘገቡ እስከ ነሀሴ 2004 ዓ.ም እየሰሩ የተገኙ 8 የህፃናት ማሳደጊያና የጉዲፈቻ አገናኝ ድርጅቶች ቢኖሩም ኤጀንሲው ክትትል እንዳላደረገባቸው እና ህጋዊ እርምጃም እንዳልተወሰደባቸው ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

72. ይህንንም በተመለከተ የኤጀንሲው ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት መልስ ቁጥሩ የተሳሳተ መሆኑን፣ በኮሚቴ ሲሰራ ቆይቶ ከዛ በኋላ ንብረት ማጣራት፣ ማስተላለፍና የማስወገድ ሥራ በዳይሬክቶሬቱ እየተሰራ የሚገኝ መሆኑን እና ለሁሉም ክልሎች ዳግም ያልተመዘገቡ በጎ አድራጎት ድርጅቶች ዝርዝር በመላክ በክልሎቻቸው እየተንቀሳቀሱ ያሉትን እንዲያጣሩ በደብዳቤ ቢያሳውቁም የአማራ ክልል በዝርዝሩ የተጠቀሱት በጎ አድራጎት ድርጅቶች ህጋዊ ሰውነት የሌላቸው መሆኑን የገለፁላቸው ሲሆን ከሌሎች ክልል ምንም ምላሽ ያላገኙ መሆኑን ገልፀዋል፡፡ የኤጀንሲው ኃላፊዎች ይህን ቢሉም የአማራ ክልል ህጋዊ ሰውነት እንደሌላቸው ከገለፁላቸው በኋላ የተደረገ ማጣራት መኖሩን ያልገለፁ መሆኑን እንዲሁም በዳግም ምዝገባ ሳይመዘገቡ እየሰሩ ተገኙ ስለተባሉት 8 የህፃናት ማሳደጊያና ጉዲፈቻ ድርጅቶች ግን ምላሽ አልሰጡም፡፡

73. የኤጀንሲው ኃላፊዎች ይህን ቢሉም የንብረት ማጣራት፣ ማስተላለፍና ማስወገድ ሥራን ኤጀንሲው በባለቤትነት እየሰራ እንዳልሆነ፣ በአሁኑ ወቅት ዳግም ያልተመዘገቡ በጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ምን ያህል መሆናቸው በትክክል የማይታወቅ በመሆኑ የተሰጠውን መልስ ለመቀበል ያዳግታል፡፡

74. ይህም በማኅበረሰብ ስም የተሰበሰበ ንብረት በአግባቡ ለተጠቃሚው ሳይደርስ በግለሰቦች እጅ እንዲቀር እና ከኤጀንሲው እውቅና ውጭ ድርጅቶች ሳይመዘገቡ ያለፈቃድ የሚሰሩበት ሁኔታ እንዲፈጠር አድርጓል፡፡

በክልሎች የበጎ አድራጎት ድርጅቶችን ለማስተዳደር የሚያስችል ህጋዊ ማዕቀፍ መኖሩን በተመለከተ

75. ኤጀንሲው ክልሎች የበጎ አድራጎት ድርጅቶችን ለማስተዳደር የሚያስችል ከፌደራሉ አዋጅ ጋር የሚጣጣም የህግ ማዕቀፍ እንዲኖራቸው ሊያደርግ ይገባል፡፡

76. በክልሎች የበጎ አድራጎት ድርጅቶችን ለማስተዳደር የሚያስችል ከፌደራሉ አዋጅ ጋር የሚጣጣም የህግ ማእቀፍ ከአማራ ብሔራዊ ክልል በስተቀር በሌሎቹ ክልሎች አለመኖሩ በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ መረጃዎች መረዳት ተችሏል፡፡

77. ይህን በተመለከተ የክትትልና ድጋፍ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ተጠይቀው በሰጡት መልስ ክልሎች በክልሉ ብቻ ለሚሰሩ በጎ አድራጎት ድርጅቶች የሚጠቀሙበት ስለሆነ ይህ ሥራ ኤጀንሲውን የማይመለከት መሆኑን እና ኃላፊነቱ የክልሎች እንደሆነ ገልፀዋል፡፡ የሥራ ኃላፊው ይህን ቢሉም የበጎ አድራጎት ድርጅቶችን በበላይነት ማተስተባበር ያለበት ኤጀንሲው በመሆኑ የተሰጠው መልስ ተቀባይነት የለውም፡፡

78. በክልሎች ተጠያቂነትን የሚያጠናክር ህጋዊ ማዕቀፍ አለመመስረቱ፣ የተደጋገፈና የተመጋገበ ስርአት እንዲኖር ኤጀንሲው አለማስተባበሩ በየክልሉ የሚንቀሳቀሱ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች በተለያየ መንገድ እንዲንቀሳቀሱ እና ወጥ የሆነ የተጠናከረ ክትትልና ቁጥጥር እንዳይኖር ያደርጋል፡፡

ኤጀንሲው ለበጎ አድራጎት ድርጅቶች እና ማህበራት ስልጠና መስጠቱን በተመለከተ፣

79. ኤጀንሲው ለበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማኅበራት እና ለክልል አስፈፃሚ አካላት በአዋጁ፣ በደንቡ እና በወጡት መመሪያዎች እንዲሁም በሂሳብ መዝገብ አያያዝና ሪፖርት አቀራረብ ላይ ስልጠና ሊሰጥ ይገባል፡፡

80. ኤጀንሲው ከተቋቋመ ጊዜ ጀምሮ ለበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት 2 ጊዜ፣ ለውጭ ኦዲተሮች የግማሽ ቀን ስልጠና የሰጠ ቢሆንም በቂ አለመሆኑን፣ በድሬዳዋ አስተዳደር እና በሀረሪ ክልል ውክልና በተሰጣቸው የክልል ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮዎች ኤጀንሲው ውክልና ከመስጠት ባለፈ ተቋማቱን የማብቃት፣ የማደራጀት፣ የማማከር፣ ተከታታይ የሆኑ ስልጠናዎች የመስጠት ስራ አልተሰራም፡፡ በክልል አስፈፃሚ አካላት መመሪያዎችና ደንቦችን በአግባቡ ያለመረዳት ችግሮች መኖራቸው እና በበጎ አድራጎት ድርጅቶች አሰራር ዙሪያ በቂ ግንዛቤ ባለማግኘታቸው የክትትልና የድጋፍ ስራውን በሚገባ እየሰሩ እንዳልሆነ፣ በኦዲቱ ወቅት መጠይቅ የቀረበላቸው የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ኃላፊዎች እና የክልል አስፈጻሚ አካላት ገልፀዋል፡፡

81. የኤጀንሲው ኃላፊዎች ስለሁኔታው ተጠይቀው በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት አስተያየት በመመሪያዎች ላይ ስልጠና ለመስጠት የተሞከረ ቢሆንም በቂ ያለመሆኑን ፣ ኤጀንሲው ውክልና ለሰጣቸው የክልል አስፈፃሚ አካላት የማብቃት ሥራን በተመለከተ የመነሻ ስልጠና መስጠቱን እና ምክር ለጠየቁ ድጋፍ እንደሚሰጡ ገልፀዋል፡፡

82. ኤጀንሲው በክልል እንዲቆጣጠሩ ውክልና ለሰጣቸው አካላት ስልጠና እና ድጋፍ ባለመጠቱ ውክልና በሰጣቸው የክልል አስፈጻሚ መ/ቤቶች አማካኝነት የተጠናከረ ቁጥጥር ማድረግ ባለመቻሉ በጎ አድራጎት ድርጅቶቹ በህጉ በመሰረት በክልሎች እየሰሩ መሆኑን ማረጋገጥ እንዳይችል አድርጎታል፡፡

II. የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራትን አዋጅ፣ ደንብ እና መመሪያዎችን ተፈጻሚ የሚያደርጉ የዘርፍ አስተዳዳሪዎች፣ ክልሎች እና ባለድርሻ አካላት በቅንጅት የሚሰሩበት የአሰራር ስርዓት እና ቀልጣፋ የመረጃ ልውውጥ ስርዓት እንዲሁም መደበኛ የመወያያ መድረክ የተዘረጋ እና ተግባራዊ የተደረገ መሆኑን በተመለከተ፤

ኤጀንሲው ከዘርፍ አስተዳዳሪዎችና ከክልል አስፈፃሚ አካላት ጋር የመግባቢያ ሰነድ(memorandem of understanding) ያለው መሆኑን በተመለከተ፤

83. የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማኅበራት ኤጀንሲ ከዘርፍ አስተዳዳሪዎች እና ከክልል አስፈፃሚ አካላት ጋር ተግባብቶና ተናቦ መስራት የሚያስችል የመግባቢያ ሰነድ (memorandem of understanding) ሊፈራረም ይገባል፡፡

84. ኤጀንሲው ከዘርፍ አስተዳዳሪዎች እና ከክልል አስፈፃሚ አካላት ጋር በፕሮጀክት ፕሮፖዛል ግምገማ፣ በጋራ የመስክ ክትትል አሰራር፣ በሪፖርት አቀራረብና ወዘተ ጉዳዮች ዙሪያ የጋራ መግባቢያ ሰነድ(mou) የሌለው መሆኑ ታውቋል፡፡

85. ከበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማኅበራት ኤጀንሲና ከፌደራል የዘርፍ አስተዳዳሪዎች ጋር የፕሮጀክት ስምምነት ተፈራርመው በየክልሎች ፕሮጀክታቸውን የሚተገብሩ በጎ አድራጎት ድርጅቶች ስለሚሰሩት ስራ የክልል የዘርፍ አስፈፃሚ አካላት መረጃ እንደማያገኙ፣ በኤጀንሲው ተመዝግበው የሚሰሩ በጎ አድራጎት ድርጅቶችን ኤጀንሲው ወዲያውኑ እንደመዘገበ የማያሳውቃቸው መሆኑ፣ እንዲሁም ኤጀንሲው የድርጅቶችን ፈቃድ ከማደሱ በፊት ከሚሰሩበት ክልል የድጋፍ ደብዳቤ ወይንም አስተያየት እንደማይጠይቅ ታውቋል፡፡

86. በሀረሪ ክልል በወጣው አዋጅ መሰረት በክልሉ የሚሰሩ በጎ አድራጎት ድርጅቶችን የመከታተልና የመቆጣጠር ስልጣን የክልሉ አደጋ መከላከልና ምግብ ዋስትና ጽ/ቤት ሲሆን ኤጀንሲው ይህን ስራ እንዲሰራ ውክልና የሰጠው የክልሉን ፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ መሆኑ ታውቋል፡፡ በዚህም ምክንያት በክልሉ የሚሰሩ በጎ አድራጎት ድርጅቶች ከክልሉ ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ወይም ከአደጋ መከላከልና ምግብ ዋስትና ጽ/ቤት ጋር አንዳንዴ ደግሞ ከሁለቱም ጋር የፕሮጀክት ስምምነት በመፈራረም ወደ ስራ እንደገቡ ለመረዳት ተችሏል፡፡ የክልሉ አደጋ መከላከልና ምግብ ዋስትና ጽ/ቤት

ከድርጅቶች ጋር የፕሮጀክት ስምምነት ቢያደርግም ክትትል እንዳላደረገ ታውቋል፡፡ ስለሆነም በክልሉ የሚሰሩ በጎ አድራጎት ድርጅቶችን እንቅስቃሴ በኃላፊነት የሚከታተላቸው አካል እንደሌለ ታውቋል፡፡

87. በእነዚህ ዙሪያ የኤጀንሲው ኃላፊዎች ተጠይቀው በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ (fact sheet) ላይ በሰጡት አስተያየት፤

- የመግባቢያ ረቂቅ ሰነድ ለሁሉም ክልሎች ተልኮ ወደ ስራ ለመግባት በሂደት ላይ መሆናቸውን፣
- በኤጀንሲው ተመዝግበው ከዘርፍ አስተዳዳሪዎች ጋር የፕሮጀክት ስምምነት ተፈራርመው በየክልሎች ፕሮጀክታቸውን የሚፈፅሙ ድርጅቶች ስለሚሰሩት ስራ የክልል የዘርፍ አስፈፃሚ አካላት መረጃ አለማግኘታቸውን በተመለከተ በአሁኑ ወቅት ከኤጀንሲው ጋር የፕሮጀክት ስምምነት የሚፈራረሙ ድርጅቶች የሌሉ መሆኑን፤
- ከኤጀንሲው ጋር ተፈራርመው በክልሎች የሚሰሩ ድርጅቶችን እንደመዘገቡ ለክልሎች የማያሳውቁ መሆኑን በተመለከተ በተሰጠው መልስ የበጎ አድራጎት ድርጅቶቹ ሲጠየቁ ማቅረብ ግዴታቸው በመሆኑ መፃፍ የሚያመጣው ጥቅም የሌለ እና አላስፈላጊ መጠባበቅ የሚፈጥር መሆኑን፣
- ፈቃዳቸውን ለማደስም ከሚሰሩበት ክልል የድጋፍ ደብዳቤ ወይም አስተያየት መጠየቅ ተገቢነት የሌለው መሆኑን፣ ድርጅቶቹ ያቀረቡት የፕሮጀክት ስምምነትና የስራ ስምምነት በቂ መሆኑን፣ እንዲሁም
- ከሀረሪ ክልል ርዕሰ መስተዳደር ጋር ተነጋግረው አግባብነት ያለውን ቢሮ መወከል ስልጣናቸው መሆኑን እና ጽ/ቤቱን የመወከል ግዴታ የሌለባቸው መሆኑን

ገልፀዋል፡፡

88. ሆኖም በኦዲቱ ከተሸፈነው ጊዜ በኋላ የሀረሪ ክልል ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ማንኛውንም በክልሉ የሚንቀሳቀሱ በጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማኅበራት ለቢሮው ተጠሪ መሆናቸውን እና የክልሉ አደጋ መከላከልና ምግብ ዋስትና ጽ/ቤትም ከጽ/ቤቱ ጋር ውል የፈፀሙትን ድርጅቶች ዝርዝር ወደ ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ መላክ እንዳለባቸው የሚገልፅ ደብዳቤ ለኦዲት ቡድኑ አቅርቧል፡፡

89. በመሆኑም በጎ አድራጎት ድርጅቶች በገቡት ውል መሰረት እየሰሩ ለመሆኑ ከሚሰሩበት የዘርፍ አስተዳዳሪ ወይም ክልል ሳይረጋገጥ ፈቃዳቸው መታደሱ ለህገወጥ አሰራር በር ይከፍታል፡፡

ኤጀንሲው ከባለድርሻ አካላት ጋር ስላለው የጋራ መድረክ እና ክትትል በተመለከተ

90. ኤጀንሲው በበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማኀበራት ዙሪያ ከባለድርሻ አካላትና ከድርጅቶቹ ጋር በዓመት ሁለት ጊዜ የጋራ የስራ ግምገማ ሊያደርግ እንዲሁም ኤጀንሲው እና የዘርፍ አስተዳዳሪዎች በዓመት ሁለት ጊዜ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች የፕሮጀክት አፈፃፀምን በተመለከተ የጋራ የመስክ ክትትል ሊያደርጉ ይገባል፡፡

91. ኤጀንሲው በሁሉም ክልሎችና ሁለቱ የከተማ አስተዳደሮች በጎ አድራጎት ድርጅቶች ለመከታተልና ለመቆጣጠር የሚያስችል አቅም ለመገንባትና ወጥ የሆነ የክትትል ስርዓት ለመዘርጋት የሚያስችል የጋራ የምክክር መድረክ ለማካሄድ በ2003 እና በ2004 በጀት ዓመታት በዕቅድ ቢይዝም አለመከናወኑ እንዲሁም ኤጀንሲው በበጎ አድራጎት ድርጅቶች አሰራር ዙሪያ ከባለድርሻ አካላትና ከድርጅቶቹ ጋር በዓመት ሁለት ጊዜ የጋራ የስራ ግምገማ እንደሚያደርግ በመሰረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ ጥናት ላይ ቢያስቀምጥም ያልተገበራቸው መሆኑ ታውቋል፡፡

92. በኦዲቱ ወቅት ቃለ-መጠይቅ ከቀረበላቸው አምስት የዘርፍ አስተዳዳሪ ሚኒስቴር መ/ቤቶች ሶስቱ (ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር፣ የትምህርት ሚኒስቴር፣ እና የሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር) እንዲሁም ከክልል ቢሮዎች ማለትም የአዲስ አበባ ጤና ቢሮ፣ የኦሮሚያ ጤና ቢሮ፣ የኦሮሚያ ግብርና ቢሮ፣ የድሬዳዋ ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ፣ የድሬዳዋ ጤና ቢሮ፣ የድሬዳዋ ሴቶች፣ ህፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ቢሮ፣ የሀረሪ ህዝብ ክልል ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ፣ የሀረሪ ሕዝብ ክልል አደጋ መከላከልና ምግብ ዋስትና ጽ/ቤት ከኤጀንሲው ጋር የጋራ የስራ ግምገማ አድርገው የማያውቁ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

93. በናሙና በታዩ የክልል አስፈፃሚ አካላት ኃላፊዎች በቀረበ ቃለ-መጠይቅ የአዲስ አበባ አስተዳደር ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ እና የአዲስ አበባ አስተዳደር ሴቶች፣ ህፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ቢሮ በዓመት አንድ ጊዜ የጋራ የስራ ግምገማ ማድረጋቸውን፣ የሀረሪ ሕዝብ ክልል ሴቶች፣ ህፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ቢሮ ከ2002-2004 ሁለት ጊዜ ብቻ፣ እንዲሁም የኦሮሚያ ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ከ2002 ወዲህ የተወሰኑ የስራ ግምገማዎችን እንዳደረጉ ይሁን እንጅ የግምገማ ሪፖርቶች ወይም ቃለ- ጉባዔዎች እንደሌሉ ገልፀዋል፡፡

94. በኦዲቱ በናሙና ከታዩ የክልል ውክልና የተሰጣቸውና የአስፈፃሚ አካላት ኃላፊዎች በቀረበ ቃለ-መጠይቅ የአዲስ አበባ ከተማ ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ እና የኦሮሚያ ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ጋር ችግር ሲፈጠር አልፎ አልፎ ከኤጀንሲው ጋር አብሮ በመሆን የጋራ የመስክ ክትትል እንዳደረጉ የገለፁ ሲሆን የሐረሪ ክልልና የድሬዳዋ ከተማ መስተዳደር ከኤጀንሲው ጋር ምንም ዓይነት የጋራ የመስክ ክትትል እንዳሌላቸው ገልጸዋል፡፡

95. የኤጀንሲው የክትትልና ድጋፍ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ተጠይቀው በሰጡት መልስ ጥቆማና ቅሬታዎች በሚቀርቡበት ወቅት ከዘርፍ አስተዳዳሪዎች (ሴክተር) ሚኒስቴር መ/ቤቶችና ከክልል አስፈፃሚ አካላት ጋር በመሆን ክትትል የሚያደርጉ ቢሆንም በታቀደው መሰረት በመደበኛነት በአመት ሁለት ጊዜ የመስክ ክትትል የማያደርጉ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

96. ኤጀንሲው ከዘርፍ አስተዳዳሪዎች (የሴክተር ሚኒስቴር መ/ቤቶች) እና የክልል አስፈፃሚ አካላት ጋር ቅንጅታዊ አሰራር እንዳይኖር ማድረጉ እንዲሁም በዕቅድ የተመራ የጋራ ክትትል አለማድረጉ በበጎ አድራጎት ድርጅቶቹ የሚታየው ችግር በወቅቱ መፍትሄ እንዳያገኝ ያደርገዋል፡፡

የበጎ አድራጎት ድርጅቶች መረጃ አያያዝን በተመለከተ

97. ኤጀንሲው የበጎ አድራጎት ድርጅቶችን መረጃ በተጠናቀረ መልኩ የእያንዳንዱን ድርጅት እንቅስቃሴ በሚያሳይ መልኩ ማለትም በተሰማሩበት የስራ ዘርፍ አይነት፣ በሚያንቀሳቅሱት የካፒታል መጠን ወዘተ በዳታ ቤዝ ሊይዝ ይገባል፡፡

98. በኦዲቱ ወቅት ኤጀንሲው የበጎ አድራጎት ድርጅቶችን መረጃ በተጠናቀረ መልኩ በዳታቤዝ በተሟላ ሁኔታ የማይዝ መሆኑ፣ ፋይሎች በተገቢው ሁኔታ የማይያዙና የማይጠበቁ መሆኑን ማለትም ፋይሎቹ የተቀዳደዱ፣ በፋይሎቹ ውስጥ የሚገኙ መረጃዎች በቅደም ተከተል ያልተቀመጡ እና በየበጎ አድርጎት ድርጅቶችን እንቅስቃሴ ወቅታዊ ሁኔታ የሚያሳይ መረጃ በተጠቃለለ መልኩ ያልተያዘ መሆኑ ታውቋል፡፡

99. የኤጀንሲው ኃላፊዎች ስለሁኔታው ተጠይቀው በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ (fact sheet) ላይ በሰጡት አስተያየት ችግሩ መኖሩ እና መሻሻል የሚገባው ቢሆንም መነሻ የሚሆን የመረጃ ቋት ያለ እና መረጃም በየፋይሉ በዴክስ ክትትል ተደርጎበት እየተቀመጠ እንደሚገኝ ገልፀዋል፡፡

100. የኤጀንሲው ኃላፊዎች ይህን ቢሉም የበጎ አድራጎት ድርጅቶች መረጃዎች በተሰማሩበት የስራ ዘርፍ፣ የፕሮጀክቱ ጊዜ፣ የሚሰሩበት አካካቢ፣ ምን ያህል ህብረተሰብ እንደሚጠቀሙ፣ በሚያንቀሳቅሱት የካፒታል መጠን፣ ቅርንጫፎች ብዛት እና የሚሰሩበት ክልል ወዘተ ተጠናቅሮ በኦዲቱ ወቅት ስላልተገኘ የተሰጠውን መልስ ለመቀበል ያዳግታል፡፡

101. መረጃዎች በአግባቡ ተጠናቅረው ካልተያዙ ተገቢውን ክትትል ለማድረግም ሆነ ወቅታዊ መረጃ ለማጠናቀርና የውሳኔ ሃሳብ ለማቅረብ አዳጋች ያደርገዋል፡፡

ክፍል ሶስት

መደምደሚያ

102. የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ኤጀንሲ በአገሪቱ ውስጥ የበጎ አድራጎት ሥራ ላይ የተሰማሩ ድርጅቶችን ፈቃድ መስጠት፣ የፕሮጀክት አፈፃፀማቸውን መከታተልና የመደገፍ አገልግሎት እንደሚሰጥ ይታወቃል፡፡ የክዋኔ ኦዲቱ ዓላማ የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ኤጀንሲ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች የፕሮጀክት አፈፃፀማቸውን ለመከታተልና ለመቆጣጠር የሚያስችል ስርዓት መዘርጋቱንና ተግባራዊ ማድረጉን እንዲሁም ከዘርፍና ከክልል አስፈፃሚ አካላት ጋር በቅንጅት እየሰራ መሆኑን ለማረጋገጥ ነው፡፡ ከዚህ ዓላማ አንፃር በኦዲቱ ወቅት የሚከተሉት ዋና ዋና ግድፈቶች ተገኝተዋል፡፡

- ኤጀንሲው የበጎ አድራጎት ድርጅቶች በፕሮጀክት ስምምነታቸው መሰረት ስለመስራታቸው በየበጀት ዓመቱ በመደበኛነት ክትትልና ቁጥጥር የማያደርግ መሆኑ፣
- የየበጀት ዓመቱን ዋና ዋና የሥራ ክንዋኔዎች እና የኦዲት ሪፖርት ለኤጀንሲው በማያቀርቡ በጎ አድራጎት ድርጅቶች ላይ በመመሪያው መሰረት እርምጃ የማይወሰድ መሆኑ፣
- ኤጀንሲው በእስትራቴጅክ እና በአመታዊ እቅድ መሰረት የበጎ አድራጎት ድርጅቶችን የመስክ ክትትል በመደበኛነት የማያደርግ መሆኑ፣
- የዴስክ (የበጎ አድራጎት ድርጅቶችን ማህደር በመመርመር) ክትትል ሥራ በዕቅዱ መሰረት የማያከናውን መሆኑ፤
- ኤጀንሲው በዴስክና በመስክ ክትትል ለታዩ ችግሮች ለበጎ አድራጎት ድርጅቶች ግብረ-መልስ የማይሰጥ መሆኑ፣
- ኤጀንሲው በዴስክና በመስክ ክትትል በታዩ ችግሮች ላይ በጎ አድራጎት ድርጅቶች የማስተካከያ እርምጃ ስለመውሰዳቸው የማይከታተል መሆኑ፣
- ከየዘርፍ አስተዳዳሪ ሚኒስቴር መ/ቤቶች ጋር የፕሮጀክት ስምምነት ያደረጉ በጎ አድራጎት ድርጅቶች የእቅድና የዕቅድ ክንውን ሪፖርት በመደበኛነት የማያቀርቡ መሆኑንና በድርጅቶች ላይ የተወሰደ የማስተካከያ እርምጃ አለመኖሩ፣
- የአሰራር ክፍተት በታየባቸው የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ላይ ኤጀንሲው ህጋዊ እርምጃ እንዲወስድ ከክልሎች ቢገለጽም እርምጃ አለመውሰዱ፣
- መመሪያን ጠብቀው በማይሰሩ ድርጅቶች ላይ መወሰድ የሚገባውን እርምጃ በወጣው የክትትልና ድጋፍ ስራ መመሪያ (ጋይድ ላይን) መሰረት ተግባራዊ አለማድረጉ፣

- ከአገር ውስጥ ምንጭ ገቢ የሚሰበስቡ በጎ አድራጎት ድርጅቶች የሰበሰቡትን ገቢ ለአላማ ማስፈፀሚያ ብቻ ማዋላቸው በኤጀንሲው ክትትል የማይደረግበት መሆኑ፤
- የሕዝባዊ መዋጮ ፈቃድ የተሰጣቸው በጎ አድራጎት ድርጅቶች መዋጮውን ባከናወኑ በ3 ወር ጊዜ ውስጥ ዝርዝር ሪፖርት ማቅረባቸውን ያልተከታተለ መሆኑ፣
- በወጪ መጋራት (cost sharing) ግልፅና ወጥ የሆነ መመሪያ ያልተዘጋጀና ተግባራዊ ያልተደረገ መሆኑ፤
- የገቢ ማስገኛ ፍቃድ ከሚመለከተው አካል ሳያወጡ የጤና አገልግሎት በክፍያ የሚሰጡ በጎ አድራጎት ድርጅቶችን በተመለከተ የክፍያ ዋጋ (price rate) አተማመን ላይ ግልፅ እና ወጥ የሆነ አሰራር የሌለ መሆኑ፣
- ከ10 ከመቶ በላይ የገቢ ምንጭ ከውጭ ያገኙ የኢትዮጵያ በጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማኅበራት ላይ በኤጀንሲው የተወሰደ እርምጃ የሌለ መሆኑ፣
- ኤጀንሲው በየዘርፉ የሚላኩ የፕሮጀክት ፕሮፖዛሎችን ለማበልፀግ የሚያስችል ወጥ ማንዋል ወይም የአሰራር ስርዓት እና የሚገመግሙ ሙያተኞች በመመደብ አገልግሎቱ በአንድ መስኮት ስር እንዲሰጥ ያላደረገ መሆኑ፣
- የዘርፍ አስተዳዳሪዎች የበጎ አድራጎት ድርጅቶችን በፕሮጀክት ስምምነት መሰረት የአጋማሽ ግምገማ (Midterm evaluation) እንደማያከናውኑ፣
- ኤጀንሲው በዳግም ምዝገባ ያልተመዘገቡ በጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማኅበራት ላይ እስከ ኦዲቱ መጨረሻ ድረስ አድራሻቸውን በማፈላለግ ንብረታቸው ያልተጣራ፣ ፈቃዳቸው ያልተመለሰ እና ህጋዊ እርምጃ ያልተወሰደ መሆኑ እንዲሁም በኤጀንሲው ይህን ለማጣራት በባለቤትነት የሚሰራ ክፍል አለመኖሩ፤
- በክልሎች የበጎ አድራጎት ድርጅቶችን ለማስተዳደር የሚያስችል ከፌዴራሉ አዋጅ ጋር የሚጣጣም የህግ ማእቀፍ ባለመኖሩ የተመጋገበና የተደጋገፈ አሰራር በተሟላ ሁኔታ መፍጠር ያልተቻለ መሆኑ፣
- ኤጀንሲው ውክልና ለሰጣቸው የክልል ቢሮዎች ውክልና ከመስጠት ባለፈ ተቋማቱን የማማከር፣ ተከታታይ የሆኑ ስልጠናዎችን የመስጠት ሥራዎች አለመስራቱ፣
- ኤጀንሲው ለበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማኅበራት በአዋጅ፣ ደንብ እና በወጡት መመሪያዎች እንዲሁም በሂሳብ መዝገብ አያያዝና ሪፖርት አቀራረብ ላይ በቂ ስልጠና ያልሰጠ መሆኑ፣
- ኤጀንሲው ከዘርፍ አስተዳዳሪዎችና ከክልል አስፈፃሚ አካላት ጋር የጋራ የመግባቢያ ሰነድ(MOU) የሌለው መሆኑ፣

- በኤጀንሲው ተመዝግበው በተለያየ ክልል የሚሰሩ በጎ አድራጎት ድርጅቶች እንደተመዘገቡ ኤጀንሲው ለክልሎች የማያሳውቅ መሆኑ፣ እንዲሁም ኤጀንሲው የበጎ አድራጎት ድርጅቶችን ፈቃድ ከማደሱ በፊት ከሚሰሩበት ክልል የድጋፍ ደብዳቤ ወይንም አስተያየት እንዲያቀርቡ የማያደርግ መሆኑ፣
- ኤጀንሲው በበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማኅበራት ዙሪያ ከባለድርሻ አካላትና ከድርጅቶቹ ጋር በዓመት ሁለት ጊዜ የጋራ የሥራ ግምገማ እና የጋራ የመስክ ክትትል የማያደርግ መሆኑን፣
- በኤጀንሲው የተመዘገቡ በጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት መረጃቸውን በተጠናቀረ መልኩ በዳታ ቤዝ በተሟላ ሁኔታ ተደራጅቶ ያልተያዘ መሆኑ፣

ታውቋል፡፡

ስለሆነም በኦዲቱ ወቅት የተገኙትን ድክመቶች እና ችግሮች ለማስወገድ ወይንም ለማቃለል አስተዋጽኦ ያደርጋሉ ብለን ያመንባቸውን የማሻሻያ ሃሳቦች በሚቀጥለው የሪፖርቱ ክፍል አቅርበናል፡፡

ክፍል አራት

የማሻሻያ ሃሳቦች

103. የበጎ አድራጎት ድርጅቶች የፕሮጀክት አፈፃፀም፣ ክትትልና ቁጥጥር በተመለከተ የወጡ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎችን ማስፈፀም የሚያስችል የአሰራር ስርዓት መዘርጋቱን እና ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ፤

- ኤጀንሲው የበጎ አድራጎት ድርጅቶችን ክትትልና ቁጥጥር የሚያደርግበት ስርዓት ሊዘረጋ እና ተግባራዊ ሊያደርግ እንዲሁም ሁሉም በጎ አድራጎት ድርጅቶች የእያንዳንዱን በጀት ዓመት ዋና ዋና የስራ ክንዋኔዎች እና የኦዲት ሪፖርት ለኤጀንሲው ማቅረባቸውን ሊከታተል በማያቀርቡት ላይ እርምጃ ሊወስድ ይገባል፡፡
- ኤጀንሲው በዴስክና በመስክ ክትትል ለታዩ ችግሮች የማስተካከያ ግብረ-መልስ ሪፖርት ለድርጅቶቹ ሊሰጥ ይገባል፡፡
- ኤጀንሲው በዴስክና በመስክ ክትትል በታዩ ችግሮች ላይ በጎ አድራጎት ድርጅቶች የማስተካከያ እርምጃ እንዲወስዱ ማድረግ አለበት፡፡
- የዘርፍ እና የክልል አስፈፃሚ አካላት የእያንዳንዱን የበጀት ዓመት ዋና ዋና የስራ ክንዋኔዎች እና የኦዲት ሪፖርት ማቅረባቸውን ሊከታተሉና ሊቆጣጠሩ የሚችሉበትን ሥርዓት ዘርግተው ተግባራዊ እንዲያደርጉ ኤጀንሲው ድጋፍ ሊሰጣቸው ይገባል፡፡
- ኤጀንሲው የበጎ አድራጎት ድርጅቶች በየበጀት ዓመቱ ከሚያወጡት ወጭ ከ70 በመቶ የማያንሰውን ለዓላማ ማስፈፀሚያ ከ30 በመቶ የማይበልጠውን ለአስተዳደራዊ ሥራ ማዋላቸውን፣ መመሪያውን ጠብቀው መሥራታቸውን ሊከታተልና ሊገመግም ይህን ተላልፈው በተገኙ በጎ አድራጎት ድርጅቶች ላይ በህጉ መሰረት ተገቢውን እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡
- አገሪቱ በበጎ አድራጎት ተግባር ላይ የተሰማሩ ድርጅቶችን በሙሉ ያካተተ የምደባ ክፍፍል (cluster) አዘጋጅቶ ሥራ ላይ ሊያውል ይገባል፡፡
- ኤጀንሲው በጎ አድራጎት ድርጅቶች ገቢ ማስገኛ ላይ ለመሰማራት እና ህዝባዊ መዋጮ ለማሰባሰብ ከኤጀንሲው እና ከሚመለከተው የመንግስት አካል የንግድ ፈቃድ ማግኘታቸውን፣ የገቢ ማሰባሰቢያ ጊዜው በተጠናቀቀ በሶስት ወር ውስጥ ከመዋጮው ጋር የተያያዘ ማንኛውንም የገንዘብ እንቅስቃሴና የሀብት ሁኔታ የሚያሳይ ሪፖርት ማቅረባቸውን፣ ከበጎ አድራጎት ሥራው የተለየ የሂሳብ መዝገብ መያዛቸውን እና

የተሰበሰበውን ገቢ ለዓላማ ማስፈፀሚያ ብቻ ማዋላቸውን የሚያረጋግጥበት ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

- ኤጀንሲው የኢትዮጵያ በጎ አድራጎት ድርጅቶች ህጉ በሚፈቅድላቸው መሰረት የገቢ ምንጫቸውን 90 በመቶ ከሃገር ውስጥ ምንጭ እና ከ10 በመቶ የማይበልጥ ከውጭ የማምጣት ህጉን አክብረው መስራታቸውን ሊከታተል ይገባል፡፡
- ከክልል አስፈፃሚ አካላት ለኤጀንሲው የሚተላለፉ ግኝቶችን በጊዜው በመከታተል የውሳኔ ሃሳብ ሊሰጡበት ይገባል፡፡
- ኤጀንሲው ፈቃድ ከማደሱ በፊት መመሪያን ጠብቀው መስራታቸውን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡
- ኤጀንሲው የወጪ መጋራት መመሪያን በአፋጣኝ በማውጣት በወጪ መጋራት ሥራ ላይ የተሰማሩ ድርጅቶች ተግባራዊ እንዲያደርጉ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ኤጀንሲው በየዘርፉ የሚላኩ የፕሮጀክት ፕሮፖዛሎችን ለማበልፀግ የሚያስችል ወጥ ማንዋል ወይም የአሰራር ስርዓት እና የሚገመግሙ ሙያተኞች በመመደብ አገልግሎቱ በአንድ መስኮት ስር እንዲሰጥ ሊያስተባብር ይገባል፡፡
- ኤጀንሲው፣ የዘርፍ አስተዳዳሪዎች እና የክልል አስፈፃሚዎች የፕሮጀክት ስምምነት ተፈራርመው ወደ ትግበራ የገቡ በጎ አድራጎት ድርጅቶችን የፕሮጀክት አፈፃፀም ለመከታተል የሚያስችል መመሪያ ሊያዘጋጅና ለየድርጅቶቹና ማኅበራቱ ሊያሰራጭ እና ተግባራዊ መሆኑን ሊከታተል ይገባል፡፡
- ኤጀንሲው በጎ አድራጎት ድርጅቶችና የጉዲፈቻ አገናኝ ኤጀንሲዎችን ትኩረት በመስጠት ሊከታተላቸው እና ተገቢውን ቁጥጥር ሊያደርግባቸው ይገባል፡፡
- ኤጀንሲው በዳግም ምዝገባ ያልተመዘገቡትን በጎ አድራጎት ድርጅቶችንና ማኅበራትን አድራሻ በማፈላለግ ንብረታቸውን ሊያጣራ፣ ፈቃዳቸውንም ሊያስመልስ እና ህጋዊ እርምጃ ሊወስድ ይገባል፡፡
- በክልሎች የበጎ አድርጎት ድርጅቶችን ለማስተዳደር የሚያስችል ከፌደራሉ አዋጅ ጋር የሚጣጣም የህግ ማዕቀፍ እንዲኖራቸው ለማድረግ እንዲቻል ኤጀንሲው ከክልሎች ጋር የጋራ መድረክ በማዘጋጀት የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራ ሊሰራና ሊያስተባብር ይገባል፡፡
- በኤጀንሲው ተመዝግበው በሀረሪ ክልል የሚሰሩ በጎ አድራጎት ድርጅቶችን በመከታተልና በመቆጣጠር በኩል ያለው ችግር እንዲፈታ ኤጀንሲው እገዛ ሊያደርግ ይገባል፡፡

- ኤጀንሲው ለበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማኅበራት በአዋጁ፣ በደንቡ እና በወጡት መመሪያዎች እንዲሁም በሂሳብ መዝገብ አያያዝና ሪፖርት አቀራረብ ላይ በቂ ስልጠና ሊሰጥ ይገባል፡፡

104. የበጎ አድራጎት ድርጅቶችንና ማህበራት ኤጀንሲ፣ አዋጆችን፣ ደንቦችን እና መመሪያዎችን ተፈጻሚ የሚያደርጉ የዘርፍ አስተዳዳሪዎች፣ ክልሎች እና ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት የሚሰሩበት የአሰራር ስርዓት እና ቀልጣፋ የመረጃ ልውውጥ ስርአት እንዲሁም መደበኛ የመወያያ መድረክ የተዘረጋ እና ተግባራዊ የተደረገ መሆኑን በተመለከተ፣

- ኤጀንሲው ከዘርፍ አስተዳዳሪዎች እና ከክልል አስፈፃሚ አካላት ጋር ተግባብቶና ተናቦ መስራት የሚያስችል የመግባቢያ ሰነድ (mou) ሊፈራረም እና በሰነዱ መሰረት መሰራቱን ሊከታተል ይገባል፡፡
- በኤጀንሲው ተመዝግበው በተለያየ ክልል የሚሰሩ በጎ አድራጎት ድርጅቶችን ኤጀንሲው ወዲያውኑ እንደመዘገበ ለክልሎቹ ሊያሳውቃቸው፣ የድርጅቶቹን ፈቃድ ከማደሱ በፊት ከሚሰሩበት ክልል የድጋፍ ደብዳቤ ወይንም አስተያየት እንዲያቀርቡ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ኤጀንሲው በበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማኅበራት ዙሪያ ከባለድርሻ አካላትና ከድርጅቶቹ ጋር በዓመት ሁለት ጊዜ የጋራ የስራ ግምገማ እና የጋራ የመስክ ክትትል ሊያደርግ ይገባል፡፡
- የዘርፍ አስተዳዳሪዎች የበጎ አድራጎት ድርጅቶችን በፕሮጀክት ስምምነት መሰረት የአጋማሽ ግምገማ (Midterm evaluation) እንዲያከናውኑ ኤጀንሲው ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ኤጀንሲው ውክልና ለሰጣቸው የክልል ቢሮዎች ውክልና ከመስጠት ባለፈ ተቋማቱን የማማከር፣ ተከታታይ የሆኑ ስልጠናዎችን የመስጠት ሥራዎች ሊያከናውን ይገባል፡፡
- ኤጀንሲው ፈቃድ ሰጥቷቸው ከዘርፍ አስተዳዳሪዎችና ከክልል አስፈጻሚ አካላት ጋር የስራ ስምምነት የሚፈራረሙ ድርጅቶችን ኤጀንሲው የመከታተል ኃላፊነት ያለበት በመሆኑ ስራዎች ሊሰሩ የሚችሉበትን መመሪያዎች በማዘጋጀትና ለሚመለከታቸው አካላት በማሰራጨት፣ የጋራ መድረኮችን በማመቻቸት የማስተባበር፣ የማደራጀት ና የክትትል ስራዎችን በመተግበር የጋራ እና የተናጠል ኃላፊነታቸው መሆኑ ታውቆ የእርምት እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡
- በኤጀንሲው የተመዘገቡ በጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት መረጃቸው በተጠናቀረ መልኩ በዳታ ቤዝ በተሟላ ሁኔታ ተደራጅቶ ሊያዝ፣ የሚያዘው መረጃም የእያንዳንዱን ድርጅት እንቅስቃሴ የሚያሳይ (በተሰማሩበት የስራ ዘርፍ አይነት፣ የሚሰሩበትን የስራ

ቦታና አድራሻ፣ በሚያንቀሳቅሱት የካፒታል መጠን ወዘተ) ሊሆን እና መረጃውን ለሚጠይቅ አካልም በወቅቱ ሊሰጥ ይገባል፡፡

105. በመጨረሻም ለበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማኅበራት ኤጀንሲ ፣ እንዲሁም በኦዲቱ ወቅት መረጃ የተሰበሰበባቸው የፌዴራል እና የክልል መ/ቤቶች፣ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች፣ ኃላፊዎች እና ሠራተኞች ስላደረጉልን የሥራ ትብብር እናመሰግናለን፡፡

አባሪ 1 <u>የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማኅበራት ኤጀንሲ ድርጅታዊ መዋቅር</u>



አባሪ 2 የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች (Evaluative Criteria)

የኦዲት የትኩረት አቅጣጫ (Audit Issues)	የኦዲት መመዘኛ መስፈርት (Evaluative Criteria)
1. የበጎ አድራጎት ድርጅቶች የፕሮጀክት አፈፃፀም፣ ክትትልና ቁጥጥር በተመለከተ የወጡ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎችን ማስፈፀም የሚያስችል ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋና ውጤታማ የአሰራር ስርዓት መዘርጋቱን እና ተግባራዊ መደረጉን መገምገም፡፡ 1.1 ኤጀንሲው የበጎ አድራጎት ድርጅቶች በየበጀት ዓመቱ ክትትልና ቁጥጥር የሚያደርግበት ስርዓት የዘረጋ እና ተግባራዊ ያደረገ መሆኑን መገምገም፣	1. የበጎ አድራጎት ድርጅቶች የተቋቋሙበትን ዓላማ ለማስፈጸም እንዲችሉ በወጣው አዋጅ ደንብና መመሪያ መሰረት የተሟላ አደረጃጀት እና በቂ የሰው ኃይል እንዲኖራቸው መደረግ አለበት፡፡
	2. ኤጀንሲው ስትራቴጂክ ዕቅድ ማዘጋጀት አለበት፡፡ የሚዘጋጀውም ስትራቴጂክ እቅድ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች የፕሮጀክት አፈፃፀምና ክትትል በተመለከተ የሚያከናውነውን ተግባር ሊያካትት ይገባል፡፡
	3. ኤጀንሲው የበጎ አድራጎት ድርጅቶች የፕሮጀክት አፈፃፀም በተመለከተ ስትራቴጂክ እቅዱን መሰረት በማድረግ አመታዊ እቅድ ማቀድና እና የእቅድ ክንውን ሪፖርት ማዘጋጀት አለበት፡፡
	4. ኤጀንሲው በሚያዘጋጀው አመታዊ የእቅድ ክንውን ሪፖርት ውስጥ በበጎ አድራጎት ድርጅቶች የፕሮጀክት አፈፃፀም ላይ የታዩ ክፍተቶች እና የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎችን ማካተት አለበት፡፡
	5. ኤጀንሲው በዳግም ምዝገባ ያልተመዘገቡ በጎ አድራጎት ድርጅቶችንና ማኅበራትን አድራሻ በማፈላለግ ህጋዊ ርምጃ መውሰድ አለበት፡፡
	6. የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማኅበራት ኤጀንሲ በየሩብ ዓመቱ በበጎ አድራጎት ድርጅቶች የመስክና የዴስክ ክትትል ማድረግ አለበት፡፡
	7. ኤጀንሲው በዴስክና በመስክ ክትትል በታዩ ችግሮች ላይ በጎ አድራጎት ድርጅቶች የማስተካከያ እርምጃ እንዲወስዱ ማድረግ አለበት፡፡
	8. በክልሎች የበጎ አድራጎት ድርጅቶችን ለማስተዳደር የሚያስችል ከፌደራሉ አዋጅ ጋር የሚጣጣም የህግ ማዕቀፍ ሊኖራቸው ይገባል፡፡
	9. የዘርፍ አስተዳዳሪዎች የበጎ አድራጎት ድርጅቶች የፕሮጀክት አፈፃፀም ለመከታተል የሚያስችል መመሪያ ሊያዘጋጁና ለየድርጅቶቹ ሊያሰራጩ ይገባል፡፡
	10. በጎ አድራጎት ድርጅቶች ገቢ ማስገኛና ህዝባዊ መዋጮ ለማድረግ ከኤጀንሲው ፈቃድ ማግኘት አለባቸው፡፡
1.2 የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ከሚመለ ከተው የመንግስት አካል ጋር የፕሮጀክት ስምምነት ማድረጋቸ ውን እና የፕሮጀክት አፈፃፀማቸው ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋና ውጤታማ መሆኑን መገምገም፣	11. ገቢ የሚያስገኙ ስራዎችን የሚሰሩ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ከበጎ አድራጎት ስራው የተለየ የሂሳብ መዝገብ እንዲይዙ መደረግ አለበት፡፡
	12. የዘርፍ አስተዳዳሪዎች ከበጎ አድራጎት ድርጅቶች ጋር በሚገቡት ስምምነት መሰረት የበጎ አድራጎት ድርጅቶች የስራ እንቅስቃሴ መከታተል፣ መቆጣጠር እና አስፈላጊውን እርምጃ መውሰድ አለባቸው፡፡
	13. ኤጀንሲው ከገቢ ማስገኛና ከህዝባዊ መዋጮ የተገኙ ገቢዎች ለዓላማ ማስፈፀሚያ መዋል አለመዋሉን ማረጋገጥ አለበት፡፡
	14. በገቢ ማስገኛ ስራ ዙሪያ የሚከናወኑ የገቢ ማመንጨት ስራዎች ድርጅቱ ከተቋቋመለት ዓላማ ጋር ተያያዥነት ሊኖራቸው ይገባል፡፡
	15. የማንኛውም በጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማኅበር ሂሳብ በየዓመቱ በተመሰከረለት ኦዲተር ወይም የውስጥ ኦዲተር ወይም ኤጀንሲው በሚሾመው ኦዲተር ሊመረመር ይገባል፡፡
	16. በጎ አድራጎት ድርጅቶች ወይም ማኅበራት የእያንዳንዱን የበጀት ዓመት ዋና ዋና የስራ ክንዋኔዎች እና የኦዲት ሪፖርት ለኤጀንሲው እንዲያቀርቡ መደረግ አለበት፡፡
	17. ኤጀንሲው ማንኛውም የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማኅበር በየበጀት ዓመቱ ከሚያወጣው ወጭ ከ70 በመቶ የማያንሰውን ዓላማውን ለማስፈፀምና ከ30 በመቶ የማይበልጠውን ለአስተዳደራዊ ስራ ማዋሉን መከታተል አለበት፡፡
	18. ኤጀንሲው የኢትዮጵያ በጎ አድራጎት ድርጅቶች ህጉ በሚፈቅድላቸው መሰረት የገቢ ምንጫቸውን 90 በመቶ ከሃገር ውስጥ ምንጭ እና ከ10 በመቶ የማይበልጥ ከውጭ የማምጣት ህጉን አክብረው መስራታቸውን መከታተልና እርምጃ መውሰድ አለበት፡፡

	19. ኤጀንሲው ለበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማኅበራት በአዋጁ፣ በደንቡ እና በወጡት መመሪያዎች እንዲሁም በሂሳብ መዝገብ አያያዝና ሪፖርት አቀራረብ ላይ ስልጠና መስጠት አለበት፡፡
	20. ኤጀንሲው በየዘርፉ የሚላኩ የፕሮጀክት ፕሮፖዛሎችን ለመገምገም የሚያስችል ወጥ ማንዋል ወይም የአሰራር ስርዓት እና የሚገመግሙ ሙያተኞች በመመደብ አገልግሎቱ በአንድ መስኮት ስር ሊሰጥ ይገባል፡፡
	21. ኤጀንሲው የዘርፍ አስተዳዳሪ ዎች፣ የበጎ አድራጎት ድርጅ ቶችና ማህበራትን የፕሮጀክት ፕሮፖዛል በሚገመግሙበት ወቅት የበጀት ድልድሉና የተፈፀሙ ወጪዎች ለአላማ ማስፈፀሚያና ለአስተዳደራዊ ስራዎች መመደብ በሚገባው ስሌት መሰረት መሆኑ መረጋገጥ አለበት፡፡
	22. ኤጀንሲው የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት የገቢ ማሰባሰቢያ በተጠናቀቀ በ3 ወር ውስጥ ከመዋጮው ጋር የተያያዘ ማንኛውንም የገንዘብ እንቅስቃሴና የሀብት ሁኔታ የሚያሳይ ሪፖርት እንዲያቀርቡ መከታተል ይኖርበታል፡፡
2.የበጎ አድራጎት ድርጅቶችንና ማህበራት አዋጆችን፤ ደንቦችን እና መመሪያዎችን ተፈጻሚ የሚያደርጉ ባለድርሻ አካላት በቅንጅት የሚሰሩበት የአሰራር ስርዐት እና ቀልጣፋ የመረጃ ልውውጥ ሥርዓት የተዘረጋ እና ተግባራዊ የተደረገ መሆኑን መገምገም፡፡	23. ኤጀንሲው ከዘርፍ አስተዳዳሪ ዎች እና ከክልሎች ጋር የበጎ አድራጎ ድርጅቶችን ለመከታተል የሚያስችል የመግባቢያ ሰነድ (MoU) ሊፈራረም እና ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡
	24. የዘርፍ አስተዳዳሪዎች የፕሮ ጀክት ሥምምነት የተፈራሙ በጎ አድራጎት ድርጅቶች በየበጀት ዓመቱ የፕሮጀክቱን አፈፃፀም የሚያሳይ እቅድና የእቅድ ክንውን ሪፖርት እንዲያቀርቡ ሊያደርጉ ይገባል፡፡
	25. የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማኅበራት ኤጀንሲ በበጎ አድራጎት ድርጅቶች ዙሪያ ከባለድርሻ አካላትና ከድርጅቶቹ ጋር በዓመት ሁለት ጊዜ የጋራ የስራ ግምገማ ማድረግ አለበት፡፡
	26. የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማኅበራት ኤጀንሲ እና የዘርፍ አስተዳዳሪዎች በዓመት ሁለት ጊዜ በበጎ አድራጎት ድርጅቶች የጋራ የመስክ ክትትል ማድረግ አለበት፡፡
	27. ኤጀንሲው የበጎ አድራጎት ድርጅቶችን መረጃ በተጠናቀረ መልኩ የእያንዳንዱን ድርጅት እንቅስቃሴ የሚያሳይ መረጃ ማለትም በተሰማሩበት የስራ ዘርፍ አይነት፣ በሚያንቀሳቅሱት የካፒታል መጠን ወዘተ በዳታ ቤዝ ሊይዝ ይገባል፡፡

አባሪ 3 በዝርዝር ኦዲት በመስክ የታዩ የዘርፍ አስተዳዳሪዎችና በጎ አድራጎት ድርጅቶች

ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር፤	
ትምህርት ሚኒስቴር፣	
ግብርና ሚኒስቴር፣	
ሴቶች፣ ህጻናትና ወጣቶች ጉዳይ ሚኒስቴር፣	
ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር	
ድሬዳዋ አስተዳደር ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ	2 በጎ አድራጎት ድርጅቶች
ድሬዳዋ አስተዳደር ጤና ቢሮ	
ድሬዳዋ አስተዳደር ሴቶች፣ ህፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ቢሮ	
ሐረሪ ህዝብ ክልል ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ	2 በጎ አድራጎት ድርጅቶች
ሐረሪ ህዝብ ክልል ሴቶች ህፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ቢሮ	
ሐረሪ ህዝብ ክልል አደጋ መከላከልና ምግብ ዋስትና ጽ/ቤት	
ኦሮሚያ ክልል ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ	
ኦሮሚያ ክልል ጤና ቢሮ	
ኦሮሚያ ክልል ግብርና ቢሮ	
አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ	4 በጎ አድራጎት ድርጅቶች
አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ጤና ቢሮ	
አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሴቶች፣ ህጻናትና ወጣቶች ጉዳይ ቢሮ	

በኦዲት ወቅት በመስክ የታዩ በጎ አድራጎት ድርጅቶች

ተ.ቁ	የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ስም	የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ዓይነት	የበጎ አድራጎት ድርጅቱ አድራሻ
1.	ወርልድ ቪዥን ኢንተርናሽናል ኢትዮጵያ	የውጭ	አዲስ አበባ
2.	ኪዩር ኢንተርናሽናል ኢንክ.	የውጭ	አዲስ አበባ
3.	ማሪስቶፕስ ኢንተርናሽናል ኢትዮጵያ	የውጭ	አዲስ አበባ
4.	ማሪስቶፕስ ኢንተርናሽናል ኢትዮጵያ	የውጭ	ድሬዳዋ ቅርንጫፍ
5.	ቴክኖሰርቭ ኢንክ	የውጭ	አዲስ አበባ
6.	ቸሻየር ሰርቪስስ ኢትየጵያ	የኢትዮጵያ ነዋሪዎች	አዲስ አበባ
7.	እድገት የህፃናት ማሳደጊያ ማሕበር	የኢትዮጵያ ነዋሪዎች	አዲስ አበባ
8.	ስለናት ማኅበር	የኢትዮጵያ ነዋሪዎች	ድሬዳዋ
9.	የኢትዮጵያ ቤተሰብ መምሪያ ማኅበር	የኢትዮጵያ ነዋሪዎች	ሐረር
10.	አቤኔዘር የህፃናት ማሳደጊያ ማኅበር	የኢትዮጵያ ነዋሪዎች	ሐረር
11.	በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን የሕፃናትና ቤተሰብ ጉዳይ ድርጅት	የኢትዮጵያ ነዋሪዎች	አዲስ አበባ

አባሪ 4 በኦዲት ወቅት ፋይላቸው የታዩ በጎ አድራጎት ድርጅቶች ዝርዝር

Ethiopian Charity

	Name	Registration Date	Registration Number.	Type (Sort)	Head Office Address
1.	TIKURET FOR ELDER WOMENT SUPPORT ASSOCIATION (TEWAS)	Jan 25,2011	2172	Charitable Society	ADDIS ABABA, W# Addis Ketema Subcity K# , H# , Phone#:0911550300 / 0911308433,

Ethiopian Resident Charities

16.	ABEBECH GOBENA YEHITSANAT KIBIKABENA LIMAT MAHIBER	Oct 23,2009	0181	Charitable Society	ADDIS ABABA, W# Arada Subcity K# 06, H# 78, Phone#:111553622 / 0111550152, email agohelma@ethionet.et,
49.	ACTOIN FOR CHANGE ETHIOPIA 2000	Nov 24,2009	1015	Charitable Society	ADDIS ABABA, W# Bole Subcity K# , H# , Phone#:0116479514 / ,
71.	ADDIS HIWOT INTEGRATED SUSTANABLE DEVELOPMENT ORGANIZATION [AHISDO]	Nov 05,2009	0445	Charitable Society	ADDIS ABABA, W# Kirkos Subcity K# 08/09, H# , Phone#:0113-206406 / ,
125.	AGRI SERVICE ---ETHIOPIA	Oct 21,2009	0124	Charitable Society	ADDIS ABABA, W# Kirkos Subcity K# 03, H# 379, Phone#:0114651212 / , email ase@ethionet.et,
171.	AMBASEL DEVELOPMENT ASSOCIATION	Nov 16,2009	0758	Charitable Society	ADDIS ABABA, W# Kirkos Subcity K# c-219, H# , Phone#:114670389 / ,
266.	Berhan integrated development and orphanage association	Feb 11,2010	1480	Charitable Society	SNNPRS, W# Badawacho K# አቡርሴ ገ/ማ, H# ገበሬ ማህበር, Phone#:911547755 / ,
343.	BRIGHT FUTURE	Jun 11,2010	1379	Charitable Society	ADDIS ABABA, W# Gullele Subcity K# 714/1, H# , Phone#:111275122 / ,
368.	CARE FOR THE POOR	Oct 27,2009	0191	Charitable Society	ADDIS ABABA, W# Nefassilk Lafto Subcity K# , H# , Phone#:113726752 / ,
412.	CIVIC ACTION ETHIOPIA	Dec 01,2009	0598	Charitable Society	ADDIS ABABA, W# Gullele Subcity K# 10, H# 087, Phone#:0911783340 / ,
0505.	CHESHIRE SERVICES ETHIOPIA	Nov 07,2009	0505	Charitable Society	ADDIS ABABA, W# Kirkos Subcity K# 02/03, H# 081, Phone#:0115505087/533287 / , email cheshire@ethionet.et,
462.	DERASH RELEIF AND DEVELOPMENT ORGANIZATION	Dec 23,2009	1237	Charitable Society	HARARI, W# Harari K# 17, H# , Phone#:0256666348 / , email derash2006@yahoo.com,
566.	ENVIRONMENTALISTS DEVELOPMENT	Nov 06,2009	0380	Charitable	ADDIS ABABA, W# Bole Subcity

	ASSOCIATION-ETHIOPIA			Society	K# 844, H# , Phone#:116460693 / ,
613.	ETHIOPIAN INITIATIVE FOR DEVLOPMENT	Oct 09,2009	0492	Charitable Society	ADDIS ABABA, W# Arada Subcity K# 17, H# , Phone#:0911683807 / , email eid@ethionet.et,
661.	FAMILY AND CHILDREN INTEGRATED DEVELOPMENT FOUNDATION(FCIDF)	Nov 24,2009	0923	Charitable Society	ADDIS ABABA, W# Kirkos Subcity K# , H# 49/50/51, Phone#:0114404038 / 0114404039,
710.	FOUNDATION FOR COMMUNITY DEVELOPMENT	Jan 21,2010	1239	Charitable Society	ADDIS ABABA, W# Bole Subcity K# 03/05, H# 149, Phone#:116188292 / , email fcd.ethiopia@yahoo.com,
734.	GELGELA INTEGRATED ORPHANS AND DESTTITUTE FAMILY SUPPORT ASSOCITATION	Oct 06,2009	0470	Charitable Society	ADDIS ABABA, W# Lideta Subcity K# 1411, H# , Phone#:0113-718931 / ,
782.	GUDINA TUMESA FOUNDATION	Oct 27,2009	0078	Charitable Society	ADDIS ABABA, W# Bole Subcity K# 14/15, H# 9999, Phone#:116464795 / ,
878.	HOPE OF FLDERS AND CHILDREN AID ORGANIZATION	Jan 08,2010	1818	Charitable Society	ADDIS ABABA, W# Kirkos Subcity K# 552, H# , Phone#:911607251 / ,
902.	IFTIN RELIEF AND DEVELOPMN ORGANIZATION (IFTIN)	Dec 28,2009	1145	Charitable Society	N/A, W# N/A K# ???, H# , Phone#:257754527 / ,
927.	INSTITUTE FOR SUSTAINABLE DEVELOPMENT	Nov 04,2009	0390	Charitable Society	ADDIS ABABA, W# Bole Subcity K# 07, H# 311, Phone#:0116186774 / 0911200834,
951.	JIGJIGA REHABILITATION AND RESETLMENT ORGANISATION	Nov 22,2009	1182	Charitable Society	SOMALI, W# Jigjiga K# 1281, H# , Phone#:913633671 / ,
998.	KNOWLEDGE ETHIOPIA	Nov 13,2009	0749	Charitable Society	ADDIS ABABA, W# Kirkos Subcity K# 15, H# 455/20, Phone#:115537272 / , email konwledgeethiopia@yahoo.com,
1095.	MEKLIT INTEGRATED DEVELOPMENT ASSOCIATION	Mar 23,2010	1719	Charitable Society	ADDIS ABABA, W# Yeka Subcity K# 06/07, H# 733, Phone#:0111239063 / ,
1262.	PARTNERSHIP FOR AFRICAN ENVIRONMENTAL SUSTAINABLITY PASE	Feb 12,2010	1345	Charitable Society	ADDIS ABABA, W# Bole Subcity K# 06/07, H# , Phone#:0913378189 / ,
1334.	REMEMBER THE POOREST COMMUNITY	Nov 11,2009	0727	Charitable Society	ADDIS ABABA, W# Arada Subcity K# 06, H# 1061, Phone#:0114162819 / 0911216269,
1550.	TESFA-COMMUNITY BASED TOURISM	Dec 21,2009	1174	Charitable Society	ADDIS ABABA, W# Arada Subcity K# 13/10, H# 573B, Phone#:0111225024 / , email tesfaacbt@ethionet.et,
1574.	THE WELL FOUNDATION	Nov 18,2009	0846	Charitable Society	TIGRAY, W# N/A K# 03, H# 109, Phone#:03443131 / , N/A, W# N/A K# 109, H# , Phone#:344443131 / ,
1623.	UNITE FOR YOUR COMMUNITY	Feb 13,2010	0815	Charitable	ADDIS ABABA, W# Gullele

	DEVELOPMENT ASSOCIATION			Society	Subcity K# 07/17, H# 7660, Phone#:911460441 / , email president@uycd.org,
1669.	WATER SHEDS ORGANIZATIONAL AND LEGAL AFFAIRS SUPPORT	Nov 25,2009	1047	Charitable Society	ADDIS ABABA, W# Arada Subcity K# 03, H# 1051, Phone#:0918761866 / , email watershedolas@yahoo.com,

Foreign Charities

	Name	Registration Date	Registration Number.	Type (Sort)	Head Office Address
1.	**CENTE FOR NATIONAL HEALTH DEV'T IN ETHIOPIA COLUMBIA UNIVERSTY**	**Dec 22,2009**	**0879**	**Foreign Charity**	**ADDIS ABABA, W# Bole Subcity K# 477, H# , Phone#:0116631050/51 / ,**
1.	Goal Ethiopia	Feb 12,2010	1472	Foreign Charity	ADDIS ABABA, W# Yeka Subcity K# 508, H# , Phone#:0116-478116 / ,
2.	HUMAN CAPITAL FOUNDATION INC.	Dec 03,2009	0561	Foreign Charity	ADDIS ABABA, W# Kolfe Keraniyo Subcity K# New, H# , Phone#:0113497037/34/39 / ,
3.	MENSCHEN FUR MENSHEN	Nov 11,2009	0438	Foreign Charity	ADDIS ABABA, W# Nefassilk Lafto Subcity K# 11, H# 1262, Phone#:0114421666/67 / ,
4.	NORWEGIAN PEOPLE'S AID(NPA)	Nov 10,2009	0684	Foreign Charity	ADDIS ABABA, W# Kirkos Subcity K# 34, H# 147, Phone#:0114665731 / , email malfrid@npaid.org, website www.npid.org
5.	SELF HELP AFRICA	Oct 12,2009	0051	Foreign Charity	ADDIS ABABA, W# Kirkos Subcity K# , H# 930/01, Phone#:0115522072/522313 / ,
6.	TECHNOSERVE INC	Dec 17,2009	0910	Foreign Charity	ADDIS ABABA, W# Yeka Subcity K# New, H# , Phone#:116623370 / ,
7.	UNIVERSITY OF CALIFORNIA SANDIEGO	Feb 21,2011	2205	Foreign Charity	ADDIS ABABA, W# Bole Subcity K# 06/14, H# 376, Phone#:0911112581 / 0917801463,
8.	WORLD VISION INTERNATIONAL ETHIOPIA	Nov 13,2009	0784	Foreign Charity	ADDIS ABABA, W# Bole Subcity K# 11, H# 518, Phone#:0116293348 / , email wve@yahoo.com,

Adoption

62	WORLD ASSOCIATION FOR CHILDREN AND PARENTS (WACAP)	Dec 25,2009	1243	Adoption	ADDIS ABABA, W# Bole Subcity K# , H# , Phone#:0116616470/1 / ,

አባሪ 5

የበጎ አድራጎት ድርጅቶች እና ማኅበራት ኤጀንሲ የድጋፍና ክትትል ተግባር የአሰራር ስርዓት ሥዕላዊ መግለጫ (Process description)



አባሪ 6 የማሪስቶፕስ ኢንተርናሽናል የ2012 እና 2011 የሂሳብ ትንታኔ

	2012		2011	
Foreign grant	132,203,045		116,124,077.00	
Local income				
service income	33,074,280.00		30,251,031.00	
Donated commodity	46,706,323.00		19,322,445.00	
Other income	6,057,743.00		5,036,098.00	
Total local income	85,838,346.00		54,609,574.00	
Total Income	218,041,391.00	184,967,111.00	170,733,651.00	140,482,620.00
Program cost	120,985,541.00	87,911,261.00	84,139,024.00	53,887,993.00
Admin cost	69,038,411.00		47,418,797.00	
Total cost	190,023,952.00		131,557,818.00	
cost from donation	156,949,672.00		101,306,790.00	
%of Admin cost from don	44%		47%	

ኪውር ኢንተርናሽናል የ2012 የሂሳብ ትንታኔ

CURE International	2012	
Foreign grant	19,074,455.87	
Income from private patients	3,779,022.39	
Other income	283,284.58	
Total income	23,136,762.84	19,357,740.45
Program cost	7,530,325.79	3,751,303.40
Admin cost	2,216,281.40	
Total cost	9,746,607.19	
cost from donation	5,967,584.80	
%of Admin cost from don	37%	